የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 35
ADDIS ABABA, 10th April, 2025


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፰/፪ሺ፲፯
የአጠቃላይ ትምህርትአዋጅ.............ገጽ ፲፰ሺ፩፻፳፪


**Content**


Proclamation No. 1368/2025
General Education Proclamation … Page 18122


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፰/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

## የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ

ትምህርት ከሰው ልጅ መብቶች በዋናነት የሚጠቀስ እንደመሆኑ መጠን ይህ መብት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ዕውቅናና ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም የትምህርት ጥራትን እና ተደራሽነትን እንዲሁም ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥር ሕግ ባለመኖሩ፤

በሕገ-መንግሥቱ፤ ሀገራችን በተቀበለቻቸው የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በቀረጸችው ፖሊሲ አጠቃላይ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች በፍትሐዊነት ተደራሽ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት የመንግሥት በመሆኑ፤

የትምህርትን ጥራት፣ አግባብነትና ፍትሐዊነት በተለይም የትምህርት ደረጃን የማውጣት ኃላፊነት የፌደራል መንግስቱ በመሆኑና ይህንም ለማስፈጸም ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

## Proclamation No. 1368 /2025

## Proclamation of General Education

Recognizing education as a fundamental human right, as emphasized by the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, there has been a lack of a comprehensive law that ensures the quality, accessibility, and equity of education;

Whereas the Constitution mandates the government to ensure that general education is equitably accessible to all citizens through various international agreements and policies adopted by our country;

Whereas the federal government is responsible for determining the quality, relevance, and equity of education, particularly at different levels of education, and the need to enact laws to enforce this mandate;




https://ethiodata.et/

የትምህርት አስተዳደርን ባልተማከለ አሠራር በማዋቀር መንግሥት፣ ኅብረተሰቡና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ለትምህርት ልማት ተገቢውን እገዛ ማድረግ እንዲችሉ የሚያበቃ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

አጠቃላይ ትምህርትን የሚመለከቱ የተበታተኑ ሕጎችና ደንቦች የነበሩ ቢሆንም መንግሥት በሚከተለው የትምህርት ልማት አቅጣጫ ተቃኝቶ የወጣ ሁለንተናዊ የአጠቃላይ ትምህርት ሕግ የሌለ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

Whereas the government, society, and other stakeholders need a legal framework to provide appropriate support for education development; by structuring education management in a decentralized manner;

Whereas, despite the existence of scattered laws and Regulations regarding general education, there is no comprehensive general education law guiding the direction of education development;

Now, therefore, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the following has been proclaimed.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፰/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ዕውቅና”** ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕግጋት፣የተቀመጡትን መስፈርት ላሟሉ የትምህርት ተቋማት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክርነት ነው፡፡

፪/ **“ተጓዳኝ ትምህርት”** ማለት መደበኛውን ሥርዓተ ትምህርት ለማጠናከር በክፍልና ከክፍል ውጭ ከአካባቢ ሁኔታዎች ጋር እየተገናዘበ በተጨማሪነት የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

## Part One
## General Provisions

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "General Education Proclamation No. 1368/2025".

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Accreditation"** means a certificate of qualification granted to educational institutions that meet the requirements set forth in this proclamation and other relevant laws.

2/ "**Co-curricula**" means supplementary education provided to strengthening the standard curriculum while being considered with environmental conditions in and out of classrooms.

https://ethiodata.et/

፫/ “**የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ**” ማለት የሥርዓተ ትምህርቱን ዓላማ፣ መርሆዎች፣ ግቦች፤ መርሐ ግብሮችና የትምህርት ዕርከኖች ያካተተ መሪ ሰነድ ነው፡፡

፬/ “**አጠቃላይ ትምህርት**” ማለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃ፤ የመካከለኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ትምህርት መርሐ ግብር የሚሰጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች ትምህርትን ያካትታል፡፡

፭/ “**የአካቶ ትምህርት**” ማለት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በአካል ጉዳት ወይንም በሌሎች ሁኔታዎች መገለልና መድሎ ሳይደረግባቸው ሥርዓተ ትምህርትን፣ የተግባቦት መንገዶችን፣ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴን እና አካባቢን በማስማማት ከሌሎች ጉዳት ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር ትምህርት የሚሰጥበትና ድጋፍ የሚደረግበት የትምህርት አቀራረብ ስልት ነው።

፮/ “**የትምህርት ተቋም**” ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕግጋት መሠረት ተመሥርቶ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጥበት ተቋም ነው፡፡

፯/ “**የመንግሥት ያልሆነ የትምህርት ተቋም**” ማለት በግል ድርጅቶች፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት፤ በማኅበረሰብ፣ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው አካላት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የተመሠረቱ የትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡

3/ "**Curriculum Framework**" means to the purpose, principles, and goals of the curriculum; it is a guiding document that includes curricula and educational levels.

4/ "**General Education**" means pre-primary, elementary, middle school, and high school education provided through formal and informal programs. It includes adult education.

5/ "**Inclusive Education**" means an educational approach in which students with special needs receive education alongside other students in a supportive environment. It ensures adaptations in curriculum, communication pathways, teaching and learning methodologies, and the educational environment without discrimination based on disability or other factors.

6/ "**Educational Institution**" means an institution that provides education and training based on this Proclamation or other relevant laws.

7/ "**Non Government Educational Institution**" means an educational institution owned by private organizations, civil society organizations, or religious institutions. It includes institutions established by the community or other appropriate bodies in accordance with this Proclamation and the Directive and Regulations enacted for its enforcement.

https://ethiodata.et/

፰/ **"ቅድመ እውቅና"** ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕግጋት ላይ ከተቀመጡት መስፈርት መሀል ቢያንስ ሰማንያ አምስት ከመቶ (፹፭/፻ ላሟሉና እስከ ቀጣዩ አንድ ዓመት ድረስ የቀረውን አስራ አምስት በመቶ ሊያሟሉ ይችላሉ ተብሎ ለታመነባቸው የትምህርት ተቋማት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ጊዜያዊ ምስክርነት ነው፡፡

፱/ **"ተማሪ"** ማለት በትምህርት ቤቶች ወይም በመምህራን ሥልጠና ተቋማት በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ ትምህርት ለመማር ተመዝግቦ በትምህርት ተቋሙ ደንብና መመሪያ መሠረት ትምህርቱን በመከታተል ላይ የሚገኝ ሰው ነው፡፡

፲/ **"መምህር"** ማለት በአጠቃላይ ትምህር ዘርፍ በትምህርት ሙያ በብቃት የሠለጠነና በማስተማርና በማሠልጠን ሥራዎች የተሰማራ ባለሙያ ሆኖ በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉ መምህራንን ይጨምራል ፡፡

፲፩/ **"የጎልማሶች ትምህርት"** ማለት ይዘቱና የትምህርት አሰጣጡ ዘዴ መደበኛ በሆነው ወይም ባልሆነው መንገድ ቢሆንም ጎልማሶች ችሎታቸውን ለማዳበር፣ ዕውቀታቸውን ለማበልጸግ ወይም የቴክኒክና የሙያ ብቃታቸውን ለማጎልመስ በታቀደ መርሐ ግብር በመደበኛ፤ በማታና በርቀት የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ የሚያልፉበት የትምህርት አሰጣጥና አቀባበል ሂደት ነው፡፡

፲፪/ **"መደበኛ ትምህርት"** ማለት በመንግሥት ወይም ዕውቅና ባገኙ ሌሎች የአጠቃላይ የትምህርት ተቋማት አማካይነት ታቅዶ በቋሚነት የሚከናወንና የሀገሪቱ ትምህርት ሥርዓት አካል የሆነና በተለያዩ ዘዴዎች የሚሰጥ መርሐ ግብር ነው፡፡

8/ "**Pre-accreditation**" means a temporary certificate of qualification granted to educational institutions that have fulfilled at least eighty-five percent of the requirements set forth in this proclamation and other relevant laws and are believed to be able to fulfill the remaining fifteen percent within one year.

9/ "**Student**" means a person enrolled in formal or non-formal education in schools or teacher training institutions and attending according to the Directive and Regulations of the educational institution.

10/ "**Teacher**" means a professional trained in the field of education, engaged in teaching and training activities, and includes teachers employed in teacher education colleges.

11/ "**Adult Education**" means the content and method of education, delivered formally or non-formally, to develop the skills of adults, enrich their knowledge, or improve their technical and professional skills; it includes evening and distance education.

12/ "**Formal Education**" means a program planned and permanently carried out by the government or other accredited general education institutions, forming part of the country's education system and provided through various methods.

https://ethiodata.et/

፲፫/ "**የሕዝብ ትምህርት ቤት**" ማለት በሕዝብ ሙሉ ባለቤትነት የሚመራ ትምህርት ቤት ማለት ነው፡፡

፲፬/ "**መደበኛ ያልሆነ ትምህርት**" ማለት ለመደበኛ ትምህርት በተጨማሪነት፣ በአማራጭነት ወይም በማሟያነት እንዲቀርብ ታቅዶ ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው ተለማጭ የሆነና የዘለቄታ ትምህርት የሚያገኙበት ሂደት ነው፡፡

፲፭/ "**ተለማጭ**" ማለት ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የሚተገበር የአሠራር ስልት (ዘዴ) ነው፡፡

፲፮/ "**የመንግሥት ትምህርት ቤቶች**" ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግሥት ባለቤትነት የሚቋቋሙና የሚተዳደሩ የትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡

፲፯/ "**ሴኩላር ትምህርት**" ማለት ከፖለቲካ ፓርቲ እና ከሃይማኖት አስተምህሮት ነፃ የሆነና በሀገር አቀፍ በፀደቀ ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

፲፰/ "**የግል ትምህርት ቤቶች**" ማለት በግለሰብ ባለሀብቶች ወይም በንግድ ማኅበራት ባለቤትነት የሚቋቋሙና የሚተዳደሩ የትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡

፲፱/ "**የሲቪል ማኅበራት ትምህርት ቤቶች**" ማለት ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች የተመሠረቱና መንግሥት ባወጣው ስታንደርድ መሠረት ሴኩላር ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው፡፡

፳/ "**በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች**" ማለት በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት የተመሠረቱና መንግሥት ባወጣው ስታንደርድ መሠረት ሴኩላር ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው፡፡

13/ "**Public School**" means a school fully owned and operated by the public.

14/ "**Non-formal Education**" means a process where students receive continuous, flexible, and sustainable education, planned as an addition, alternative, or supplement to formal education.

15/ "**Flexible**" means a strategy of operation adapted to actual conditions.

16/ "**Government Schools**" means educational institutions owned and operated by the Federal or Regional Government.

17/ "**Secular Education**" means an education system that is independent of any political party or religious doctrine and is provided based on a nationally approved curriculum.

18/ "**Private Schools**" means educational institutions established and managed by individual investors or business associations.

19/ "**Civil Society Schools**" means institutions established by non-profit organizations that provide secular education according to standards issued by the government.

20/ "**Schools owned by Religious Institutions**" means institutions established by various religious bodies that provide secular education according to standards issued by the government.

https://ethiodata.et/

፳፩/ "**ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች**" ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቋቁመው ወይም ተመዝግበው በሌላ ሀገር ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው።

፳፪/ "**በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት**" ማለት በውጪ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይንም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ሥርዓት ትምህርት መሠረት የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

፳፫/ "**በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት**" ማለት በኢትዮጵያ የሚኖሩ የውጭ ዜጎች ልጆቻቸውን በሀገራቸው ሥርዓት ትምህርት ለማስተማር የሚያቋቁሙት ትምህርት ቤት ነው።

፳፬/ "**የተፋጠነ ዝውውር**" ማለት ፈጣን የአእምሮ እድገትና የመማር ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት ካላንደሩን ሳይጠብቅ የሚደረግ የክፍል ክፍል ዝውውር ነው፡፡

፳፭/ "**የተፋጠነ ትምህርት**" ማለት በተለያዩ ምክንያቶች በመደበኛው ትምህርት መርሃ-ግብር ተጠቃሚ ያልሆኑ ልጆች ተለማጭ፣ ከእድሜያቸው ጋር ተስማሚ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት እና በተፋጠነ የትግበራ ስልት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በፍትሐዊነት ተደራሽ ለማድረግ የሚተገበር አማራጭ የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ነው።

፳፮/ "**ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ስራዎች**" ማለት ማናቸውም የንግድ ስራ ሲሆን እንደ ጫት ማስቃም፣ ሺሻ ቤቶች፣ መጠጥ ቤት የቀንና የምሽት ጭፈራ ቤት ንግዶችን ያጠቃልላል፡፡

21/ "**International Schools**" means institutions established or registered in Ethiopia that provide educational services according to the curriculum of another country.

22/ "**Ethiopian Community Schools Abroad**" means institutions established by Ethiopians or descendants of Ethiopians living abroad, providing educational services according to the Ethiopian curriculum.

23/ "**Foreign Community Schools in Ethiopia**" means schools established by foreigners living in Ethiopia to educate their children according to their home country's curriculum.

24/ "**Accelerated Promotion**" means a classroom transfer done without waiting for the educational calendar for those who have high-achieving and learning skills students.

25/ "**Accelerated Learning**" is an alternative education delivery method that applies for various reasons to children who do not benefit from the regular education program through a flexible, age-appropriate curriculum and accelerated implementation strategy to make quality education fairly accessible.

26/ "**Indecent Businesses**" means any business such as chaat picking area, hookah bars, pubs, and nightclubs.

https://ethiodata.et/

፳፯/ **“አንኳር ትምህርት”** ማለት ከመሠረታዊ ትምህርቶች ውስጥ ሌላውን ትምህርት ለመማር አጋዥና መሠረት የሚሆን ነው፡፡

፳፰/ **“የሙያ ፍቃድ”** ማለት መምህራን፣ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች ለሙያው የሚስፈልገውን የብቃት ደረጃ አሟልተው ሲገኙ የሚሰጥ ፍቃድ ነው፡፡

፳፱/ **“መሠረታዊ ትምህርት”** ማለት በአጠቃላይ ትምህርት ውስጥ ተካቶ የሚሰጥ የትምህርት አይነት ነው፡፡

፴/ **“ቢሮ”** ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋሙ ክልሎች ትምህርት ቢሮዎች ሲሆኑ በተቋቋሙበት ቻርተር መሰረት የከተማ አስተዳደር የሆኑ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎችን ይጨምራል፡፡

፴፩/ **“መንግሥት”** ማለት እንደነገሩ ሁኔታ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ሲሆን በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የፌደራሉ መንግሥት አባል የሆነ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትንም ይጨምራል፡፡

፴፪/ **“ማኀበራዊ የክፍል ዝውውር”** ማለት መምህሩ የተማሪውን ክፍተት እየለየ የሚገነባበትና የሚያበቃበት እንዲሁም ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ የሚያሸጋግርበት ሂደት ነው፡፡

27/"**Core Subject**" means a fundamental and essential type of subject knowledge that forms the basis for understanding and learning subsequent lessons in basic subjects.

28/ "**Professional License"** means a license granted to teachers, educational leaders, and professionals upon demonstrating that they have met the required level of competency for their respective profession.

29/ "**Basic Subject**" means a type of subject that is offered as part of a general education curriculum.

30/ "**Bureau**" means regional education bureau established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Republic of Ethiopia and includes the education offices of Addis Ababa and Dire Dawa city administrations, which are city governments according to their respective charters.

31/ "**Government**" means the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the national regional governments, which are members of the Federal Government according to the constitution.

32/ " **Students Social Promotion**" means the process by which the teacher addresses and reduces the achievement gap among students, facilitating their progression to the next grade level.

https://ethiodata.et/

፴፫/ **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም የትምህርት ሚኒስትር ነው፡፡

፴፬/ "**ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ**" ማለት ልዩ ችሎታና ላቅ ያለ ትምህርትና ሥልጠና የመቀበል አቅም ነው፡፡

፴፭/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተቋቋሙትንና በአንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ /ሠ/ መሠረት አዲስ የተደራጁትን ክልሎች፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ድሬደዋ አስተዳደርን የሚያጠቃልል ነው፡፡

፴፮/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፴፯/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ አጠቃላይ ትምህርትን በተመለከተ በሁሉም የፌደራልና የክልል የትምህርት ተቋማት፣ እንደዚሁም በትምህርት አቅርቦትና አቀባበል ረገድ በሀገሪቱ በተሰማሩ መንግስታዊ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትና በውጭ ሀገር በተቋቋሙ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በኢትዮጵያ የሀገር የመከላከያ ሠራዊት፣ በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር፣ በስደተኛ ጣቢያዎችና በሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

33/ **"Ministry" or "Minister"** means the Ministry of Education or the Minister of Education, respectively.

34/ **"Talented and Gifted"** means the ability to receive special skills and advanced education and training to mean special talent and abandonment"

35/ **"Regions"** means the regions established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. In accordance with Article 47, Sub-Article 3, Letter (e), it includes the newly organized regions, the Addis Ababa City Government, and the Dire Dawa Administration.

36/ **"person"** means a natural or juridical person.

37/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This proclamation applies to general education in all federal and regional educational institutions, as well as to governmental and non-governmental bodies engaged in the provision and reception of education in the country and Ethiopian social education institutions established abroad.

2/ It applies to all schools run by the Ethiopian Defense Forces, Prisons Administration, refugee centers, and other government institutions.

https://ethiodata.et/

**፬. <u>የአጠቃላይ ትምህርት መርሆዎች</u>**

የሀገሪቱ አጠቃላይ ትምህርት አቅርቦት፣ ስርጭትና አስተዳደር በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡-

፩/ ትምህርትን በእኩልነትና በፍትሐዊነት ተደራሽ ማድረግ፣

፪/ የትምህርት ጥራት እና አግባብነት ማረጋገጥ፣

፫/ የአጠቃላይ ትምህርት የትምህርት አመራርና አስተዳደር ባልተማከለና በዲሞክራሲያዊ ውሳኔ አሰጣጥና በተጠያቂነት መርሕ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ፣

፬/ በትምህርት ተቋማት ከሚፈጸሙ ማናቸውም ዓይነት አድሏዊ አሠራሮች መጠበቅ፣

፭/ የተማሪዎችን በነጻነት የማሰብ፣ የመጠየቅና የመመራመር ጥረት ማበረታታት፣ እንደዚሁም ለቀጣይ ሁለንተናዊ ዕድገታቸው የሚያግዙ ክህሎቶችን፣ የሥነ ምግባር ደንቦችንና ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣

፮/ በተማሪዎች መካከል የሰላም፣ የአብሮነት እና የመቻቻል መንፈስ ማዳበር የሚያስችል የትምህርት አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፣

፯/ መልካም አስተዳደርን፣ ማኅበራዊ ተሳትፎ እና አብሮነትን መሠረት ባደረገ መልኩ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ የግሉ ዘርፍና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉበት የትምህርት ልማትና አመራር ማመቻቸት፣

፰/ የትምህርት አቅርቦት ሀብትንና ቁሳቁስ አጠቃቀምን ወጭ ቆጣቢ ማድረግና ለሁሉም ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የሚዳረስበትን ሁኔታ መፍጠር፣

**4. <u>Principles of General Education</u>**

The provision, distribution, and management of general education in the country shall be based on the following guiding principles:

1/ Making education accessible with equality ,

2/ Ensuring the quality and relevance of education,

3/ Basing education leadership and management of general education on the principles of decentralized and democratic decision-making and accountability,

4/ Protecting against any kind of discriminatory practices carried out by educational institutions,

5/ Encouraging students to think freely, inquire, research, and develop skills, ethics, and abilities for their overall development,

6/ To ensure the provision of education among students that fosters the development of a spirit of peace, solidarity, and tolerance,

7/ Facilitating educational development and leadership in which parents, guardians, community members, the private sector, and other stakeholders can contribute in a manner based on good governance, social participation, and solidarity,

8/ Ensuring the cost-effective use of educational resources and materials and making them accessible to all equitably,

https://ethiodata.et/

፱/ ሀገራዊ የትምህርት ሥርዓትን ከሃይማኖት እና ከፓርቲ ፖለቲካ ወገንተኝነት መለየት፣

፲/ ለሀገር በቀል እውቀቶች ልዩ ትኩረት መስጠት፣

## ፭. የአዋጁ ዓላማዎች

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ዋንኛ ዓላማ ትምህርትን በመላ ሀገሪቱ በእኩልነትና በፍትሐዊነት ተደራሽ በማድረግ፣ የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በማረጋገጥ፣ ተማሪዎች በዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ታንጸው መልካም ዜጎችና ኃላፊነት የሚሰማቸው የህብረተሰቡ አካል ይሆኑ ዘንድ የተሟላ ስብዕና እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡

(ሀ) እያንዳንዱ ተማሪ ለመጪው ሕይወቱና ለቀጣዩም የትምህርት ዕርከን የተዘጋጀ መሆኑን የሚያረጋግጥ በዝንባሌ፣ በፍላጎትና በሀገራዊ የትምህርት አቅጣጫ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ለ) የማንበብ፣ የመጻፍና የስሌት ክህሎትን በማስፋፋት በተለይም የሴቶችን፣ የገጠር ነዋሪዎችን፣ የአርብቶ አደሮችን፣ የአካል ጉዳተኞችንና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሌሎች ተገቢውን የትምህርት ልማት ያላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን እና ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት አቅርቦት ማሻሻል፤

9/ Separating the national education system from religious education and party politics,

10/ Giving special attention to indigenous knowledge,

## 5. Objectives of the Proclamation

1/ The primary objective of general education is to ensure equal and fair access to education across the country, guaranteeing its relevance and quality. It aims to help students develop a well-rounded personality, equipping them with the knowledge, skills, and attitudes necessary to become responsible citizens and contributing members of society. this proclamation shall have the following detailed purpose.

a) Ensuring that every student is prepared for their future life and the next level of education, receiving education based on their inclinations, needs, and national educational direction;

b) Expanding reading, writing, and computational skills, with a particular focus on improving educational provisions for women, rural residents, pastoralists, people with disabilities, and other students with special needs who have not received adequate educational development, as well as those with special talents or who have been abandoned;

https://ethiodata.et/

(ሐ) ጥራት ያለው የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ ትምህርትን የበለጠ ተደራሽ ማድረግ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመካከለኛና ከፍተኛ ሙያ ዝግጅት መሠረታዊ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጥ መሆኑን ማመላከት፤

c) Making quality pre-primary education, primary, and middle level education more accessible, and indicating that middle level education lays the foundation for middle and higher career preparation;

(መ) በእያንዳንዱ ተማሪ አመለካከት ውስጥ የማኅበራዊ ኃላፊነት መንፈስ፣ የሥራ ክቡርነት፣ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ የሕግ የበላይነትን፤ ልዩነቶችን የማክበር፤ የሰብዓዊ መብት፣ የሰብዓዊ ክብርና የዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እንዲሠርጽ ማድረግ፤

d) Instilling in every student's attitude the spirit of social responsibility, dignity of work, patriotism, respect for differences, rule of law, human rights, human dignity, and democratic thinking;

(ሠ) ተማሪዎች አካባቢያቸውን የመረዳት፣ የመመራመርና የመፍጠር፣ የማድነቅና የመምራት ችሎታቸውን ማዳበር፤

e) Developing students' ability to understand, research, create, appreciate, and engage with their environment;

(ረ) በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሁሉም ዜጎች ትምህርት በፍትሐዊ መልኩ እየተዳረሰ መሆኑን ማረጋገጥ፤

f) Ensuring that education is equally accessible to all citizens, regardless of their location, throughout the country;

(ሰ) የሁሉም የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን፤ ማኅበራዊ እሴቶችን፤ እንዲሁም ሁሉንም በጐ የሰው ልጅ ሥራ ውጤቶችን ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚያስችል የትምህርት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፤

g) Preserving the historical and cultural heritage of all the nations, nationalities, and peoples of the country; social values; and implementing an education system ;

https://ethiodata.et/

**፮. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ የተደነገጉት የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባሮች እንደተጠበቁ ሆኖ ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ የትምህርት ደረጃ ማስጠበቅ፣ የትምህርት ጥራትንና አግባብነት ማረጋገጥና በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አስተዳደርና አመራር አካላት ተግባርና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል የሚኒስቴሩ ኃላፊነት ነው፡፡

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባሮች ያከናውናል፡-

(ሀ) ሀገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መቅረጽና ሥራ ላይ ማዋል፣ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች፣ ሌሎች ልዩ ልዩ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ሀገር አቀፍ የትምህርት ስታንዳርዶችን ማውጣት፤

(ለ) ሀብት ወይም የገቢ ምንጭ ማፈላለግና ለክልል የትምህርት አስተዳደር አካላት ቴክኒካዊና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፤

(ሐ) የሥርዓተ-ትምህርት ትግበራ ዓቢይ ኮሚቴ ማቋቋም፣ መመሪያና ደረጃ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎችን መመልመልና ማዘጋጀት፣ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤ የሁለተኛ ደረጃ የመማሪያ እና ማስተማሪያ መጻሕፍት ማተምና እስከ ክልል ዋና ከተማ ድረስ ማድረስ፤

**6. The Powers and Duties of the Ministry**

1/ The powers and functions of the Ministry, as provided by Proclamation No. 1263/2021 the definition of the powers and functions of the executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, are upheld. It is the responsibility of the Ministry to maintain the national level of general education, ensure the quality and relevance of education, and oversee and monitor the functioning and responsibilities of governing and leadership bodies at all educational levels.

2/ Notwithstanding to Sub Article (1) of this Article, the Ministry shall :

a) Formulating and implementing a national education and training policy, developing strategies to implement the policy, creating guidelines, developing diverse documents, and enacting national education standards;

b) Identifying sources of wealth or income and providing technical and professional support to state educational management bodies;

c) Establishing a steering committee for the implementation of the curriculum, recruiting and preparing experts to develop guidelines and standards, developing a curriculum framework, publishing secondary textbooks, and ensuring their delivery to regional states capitals;

https://ethiodata.et/

(መ) በክልል ጥያቄ ሲቀርብለት የ፪ኛ ደረጃ መጻሕፍት ማሳተምን ለክልል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ የሚነሱ ችግሮች መወገዳቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ነፃና የግዴታ ትምህርት በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች በተሟላ መልክ ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፤

፬/ ትምህርትን በአደጋ ጊዜ ማስቀጠል የሚቻልበት ሁኔታን ሚኒስቴሩ መመሪያ በማውጣት እንዲተገበር ማድረግ፤

፭/ የዓለም አቀፍና የማህበረሰብ ትምህርት ቤቶችን ማስተዳደር፤

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙባቸው ክልሎች ከሚኒስቴሩ ጋር በመቀናጀት የማስተዳደር ሚና እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

፯. <u>የክልሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃ፣ ጥራትና አግባብነትን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ክልሎች ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉባቸው፡፡

(ሀ) ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውንና በሚኒስቴሩ የሚወጡትን ብሔራዊ የትምህርት ደረጃ ማስጠበቂያ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤

d) Upon request from a state, delegating the publication of secondary textbooks to the respective state.

3/ Ensuring that issues related to maintaining the quality of education are addressed and monitoring the full implementation of free and compulsory education across all parts of Ethiopia;

4/ In the event of an emergency that impacts the continuation of education, the Minister shall implement a Directive to address the situation;

5/ Managing international and community schools;

6/ The provisions in Sub-Article (5) of this Article outline the Ministry's role in managing international schools, with integration into the regional jurisdictions where the schools are located.

7. <u>Powers and Responsibilities of the States</u>

1/ Based on the constitutional responsibility granted to the Ministry regarding the level, quality, and relevance of general education, states shall have the following functions and responsibilities.

a) Implementing the national education and training policy and adhering to the national education standards and guidelines issued by the Ministry;

https://ethiodata.et/

ለ)ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው ስታንዳርዶች መሠረት በየክልሎቻቸው አጠቃላይ የትምህርት ተቋማትን መመሥረት፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን መቆጣጠር፤

(ሐ) በሁሉም እርከኖች ያሉ የመንግሥት የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን (ከ፩ኛ እስከ ፰ኛ ክፍል) እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን (ከ፱ኛ እስከ ፲፪ኛ ክፍል) ማስተዳደር፤

(መ) ደመወዝ መክፈል፣ ዝውውር፣ ዕድገትና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ጨምሮ በሁሉም የመንግሥት አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት የሚገኙ መምህራንን፣ የትምህርት አመራር እና ሠራተኞችን ማስተዳደር፤

(ሠ) የቅድመ አንደኛ፤ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ መጻሕፍት ማተምና ማሰራጨት፣ የሁለተኛ ደረጃ መማሪያ እና ማስተማሪያ መጻሕፍት ማሠራጨት እንዲሁም የትምህርት ቤቶቹን ህንፃዎችና ቋሚ ንብረቶች ማስተዳደር፤

(ረ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ትምህርትን በአደጋ ጊዜ እንዲቀጥል ማድረግ፡፡

፪/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክልሎች በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በዞን፣ ክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ የትምህርት አስተዳደር አካላት በውክልና መስጠት ይችላሉ፡፡

፫/ ክልሎች በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት አስተዳደር አካላት በሚመለከቷቸው አካባቢዎች የትምህርትና ሥልጠና አካላትን የማቋቋምና እነዚህ አካላት ሥራቸውን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እያከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

b) Establishing general educational institutions within their respective regions in accordance with the standards set by the Ministry, and regulating their functioning and responsibilities;

c) Managing government pre-primary, primary, middle (grades 1 to 8), and high schools (grades 9 to 12) at all levels;

d) Administering teachers, educational leadership, and staff at all government general educational institutions, including handling salaries, transfers, promotions, and disciplinary matters;

e) Developing and disseminating textbooks for pre-primary, primary, and middle schools; ensuring the distribution of secondary school textbooks and instructional materials; and managing school buildings and permanent assets;

f) Ensuring the continuation of education during emergencies in accordance with Directives issued by the Ministry.

2/ When necessary, states may delegate the functions and responsibilities assigned to them under this decree to educational governing bodies at the zone, sub district, district, and kebele levels.

3/ States shall be responsible for establishing educational and training bodies at all levels and ensuring that these bodies operate in accordance with the Directives of the Ministry.

https://ethiodata.et/

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት በክልል ትምህርት ቢሮ እና በሁሉም እርከኖች ያሉትን የትምህርት ተቋማትን ማስተዳደር፡፡

፭/ በክልላቸው የሚገኙ የዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት ማስተዳደር፡፡

**፰. የመማር መብት**

፩/ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ በዚህ አዋጅ እንዲሁም በሌሎች አግባብ በሆኑ ሕጎች እንደተመለከተው መንግሥት ጥራት ያለው ትምህርትን ለዜጎች ሁሉ የማዳረስ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የመንግሥት አካላት፣ የሲቪል ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ፣ ግለሰቦችና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች የዜጎች የመማር መብትን የማክበርና እንዲተገበር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

**፱. በትምህርት ረገድ የሚኖር አድልኦን ስለማስወገድ**

፩/ ትምህርት ከማንኛውም ዓይነት አድሏዊ አሠራሮች የጸዳ መሆን ያለበት ሲሆን ይህም በብሔረሰብ፣ በማኅበራዊ መሠረት፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነት ወይም በሌሎች የልዩነት መሠረቶች የሚደረጉ መድልዎችን ያካትታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች የተመለከቱት አፈጻጸሞች በአድሏዊ አሠራርነት አይመደቡም፣

4/ States shall administer educational institutions through their respective State Education Bureaus and at all levels in accordance with this decree.

5/ States shall manage international schools within their jurisdiction in coordination with the Ministry of Education.

**8. Right to Education**

1/ According to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, this Proclamation, and other relevant laws, the government should provide quality education to all citizens.

2/ Government bodies, civil society organizations, the private sector, individuals, and other members of society shall obliged to respect and implement this right of citizens to education in every possible way.

**9. Eliminating Discrimination in Education**

1/ Education should be free from any kind of discrimination based on ethnicity, social status, skin color, gender, age, language, religion, disability, political bias, or other grounds of difference.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the following practices shall not be classified as discriminatory ,

https://ethiodata.et/

(ሀ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸውና እንዲሁም ልዩ ተሠጥዖና ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ተብለው ተለይተው የሚቋቋሙ የትምህርት ተቋማት፣

(ለ) በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ የተቀመጡ መስፈርትን በማሟላት የሚመሠረቱና የሚካሄዱ የግል የትምህርት ተቋማት፣

(ሐ) ከፊል ወይም ሙሉ የነጻ ትምህርት ማግኘትንና የትምህርት ቤት ክፍያን አስመልክቶ በዜጎችና በውጭ ሀገር ዜጎች መሀል የሚፈጸሙ የአሠራር ልዩነቶች፣

**፲. የአጠቃላይ ትምህርት ዕርከኖች**

የአጠቃላይ ትምህርት ዕርከኖች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ/ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት፣

ለ/ ከ፩ኛ ክፍል እስከ ፮ኛ ክፍል የሚሰጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣

ሐ/ በ፯ኛ እና ፰ኛ ክፍል የሚሰጥ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት፣

መ/ ከ፱ኛ ክፍል እስከ ፲፪ኛ ክፍል የሚሰጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣

**፲፩. በአጠቃላይ ትምህርት ለሚሳተፉ የግልና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ዘርፎች የሚደረግ የመንግሥት ድጋፍ**

፩/ አጠቃላይ ትምህርትን አስመልክቶ የሚያወጣቸውን የደረጃ መስፈርቶች ሕግጋት አክብረው እስከሠሩ ድረስ የግል ባለሀብቶችና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በዘርፉ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ይደግፋል፣ ያበረታታል፡፡

a) According to the Directives issued by the Ministry, educational institutions established for men, women, disabled students, students with special needs, and students with special gifts and talents,

b) Private educational institutions that are established and run by meeting the criteria set at the national or regional level,

c) Differences between nationals and foreign nationals regarding access to partial or full free education and school fees,

**10. Levels of General Education**

The levels of general education are as follows:

a) Pre-primary education,

b) Primary education from grade 1 through grade 6 ,

c) Intermediate level education provided in 7th and 8th grade,

d) Middle-level education provided from grade 9 through 12,

**11. Government Support for Private and Non-Governmental Sectors in General Education**

1/ The government supports and encourages the participation of private investors and non-governmental entities in the sector as long as they comply with the standards and regulations issued by the government regarding general education.

https://ethiodata.et/

፪/ አግባብ ያላቸውን ሕግጋት መሠረት በማድረግ መንግሥት ተጨባጭ በሆነ የትምህርት ልማት ዘርፍ ለሚሳተፉ ባለሀብቶችና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በሀገሪቱ የኢንቨስትመንት ሕግና አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት ማበረታቻዎችን ያደርጋል፡፡

፫/ መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት ምዝገባ፣ ዕውቅናና ቁጥጥር አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ እንደሁኔታው የክልል መንግሥታት በሚያወጧቸው ሕጎች መሠረት ይከናወናል፡፡

2/ Based on the relevant laws, the government will provide incentives to investors and non-governmental entities involved in the education development sector in accordance with the country's investment law and relevant laws.

3/ The registration, accreditation, and inspection of non-governmental educational institutions shall be carried out in accordance with the relevant provisions of this Proclamation, the Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation, and the laws issued by regional governments as applicable.

## ፲፪. <u>የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት አመሠራረትና መልሶ አደረጃጀት</u>

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት፣ በሕዝብ፣ በግል ባለሀብቶች፣ በሕግ አግባብ በተቋቋሙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ በውጭ ሀገር ማኅበረሰብ አባላት ወይም ሚኒስቴሩ በሚፈቅድላቸው ተቋማት ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች መሠረት በማሟላት አንድ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም መልሶ ሊደራጅ ወይም ሊፈርስ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተቋቋመ የመንግሥት አጠቃላይ ትምህርት ተቋም ሕጋዊ ሰውነት የሚኖረው ሲሆን፣ ከዚህ አቋሙ የሚመነጩ ተግባሮችን ማከናወን ይችላል፡፡

## 12. <u>Establishment and Reorganization of General Education Institutions</u>

1/ General education institutions can be established by the government, by the public, by private investors, by charitable organizations established by law, foreign community members, or institutions approved by the minister or their representative.

2/ A general education institution may be reorganized or dissolved based on the criteria set by the minister or their representative.

3/ A government general education institution established in accordance with the provisions of this proclamation shall have legal personality and may perform duties arising from this status.

https://ethiodata.et/

፬/ የመንግሥት ያልሆኑ አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ችሎታ ካቋቋማቸው ግለሰብ፣ የንግድ ማኅበር፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ ወይም በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው አካል ሕጋዊ ሰውነት የሚነሳ ይሆናል፡፡

፭/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ የመንግሥት የትምህርት ተቋማት በሁሉም መልኩ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተቋቋሙ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

፮/ የመንግሥት ያልሆኑ አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚገለጽ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንደገና መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ነጻና የግዴታ ትምህርት

**፲፫. ነጻና የግዴታ ትምህርትን የሚመለከቱ አጠቃላይ ድንጋጌዎች**

፩/ ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ማንኛውም ሕጻን በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርትን በነጻ የመማር መብትና ትምህርቱንም የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ዜጋ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በነጻ የመማር መብት አለው፡፡

፫/ አንድ ሕጻን በሚኖርበት አካባቢ ባሉ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘቱን ማረጋገጥ የመንግሥት ኃላፊነት ነው፡፡

4/ The ability of non-governmental general education institutions shall arise from the individual, business association, charity organization, or legal entity that owns and manages them.

5/ Government educational institutions established before the issuance of this proclamation shall be deemed to have been established by this proclamation in all respects.

6/ Non-governmental general education institutions must be re-registered according to the schedule specified in the Directive issued by the Minister or their representative. The Directives issued by the Ministry will determine the schedule.

## Part Two
## Free and Compulsory Education

**13. Free and Compulsory Education**

1/ Any child of school age in government schools at the pre-primary level has the right to free primary and middle-level education and the obligation to attend school.

2/ Every citizen has the right to free middle-level education in government schools.

3/ Pre-primary education in government schools in the area where a child lives will be the government's responsibility to ensure that primary, middle, and middle leevel education is available.

https://ethiodata.et/

፬/ አንድ ተማሪ ከሚማርበት ትምህርት ቤት በተለያዩ ምክንያቶች የመኖሪያ አድራሻውን ሲቀይር ወደሌላ ትምህርት ቤት ተዛውሮ የመማር መብት አለው፡፡

፭/ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሚቀበሏቸው ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና መስጠት የሚችሉት ተማሪውን በየትኛው የትምህርት ክፍል መቀበል እንደሚኖርባቸው ማረጋገጥ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ብቻ ነው፡፡

፲፬. **<u>የትምህርት ክፍያ ስላለመኖሩ</u>**

፩/ በማንኛውም የመንግሥት አጠቃላይ የትምህርት ተቋም በመደበኛው የትምህርት መርሐ ግብር ከሚካፈል ተማሪ፣ ከወላጆቹ ወይም ከአሳዳጊዎቹ የትምህርት ክፍያ፣ የመማሪያ መጻሕፍት ዋጋ ወይም የመመዝገቢያ ክፍያ መቀበል የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ክልሎች በሚያወጡት ህግ መሰረት ለሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች የሚውል መጠነኛ ክፍያ ከተማሪ ወላጆች የመክፈል አቅም ጋር በተጣጣመ መልኩ ሊያስከፍሉ ይችላሉ።

፫/ በንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ የተመለከተው ቢኖርም ይህን አላሟላህም ተብሎ ተማሪው ከትምህርት ገበታው እንዲለይ ማድረግ አይቻልም፡፡ ለሚደረጉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች ሁሉ ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት ይኖርበታል ፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በዜግነት ኢትዮጵያዊ ካልሆነ ተማሪ በመንግሥት የትምህርት ተቋማት የትምህርት ክፍያ እንዲፈጽም ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፍቃድ ያገኙ ስደተኛ ሕጻናት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አጠቃላይ ትምህርትን ያለክፍያ የመከታተል መብት አላቸው፡፡

4/ A student has the right to transfer to another school when they change their residential address for various reasons.

5/ Government schools can only give entrance exams to admitted students when they need to confirm the student's admission in a specific department.

**14. <u>Prohibition of Tuition Fees</u>**

1/ It is prohibited to receive tuition fees, textbook fees, or registration fees from a student participating in the regular education program of any government general education institution, or from their parents or guardians.

2/ According to the laws issued by the regional governments , a modest fee for other educational equipment can be accepted based on the ability of the student's parents to pay.

3/ Despite what is mentioned in Sub Article (2), it is not permissible for the student to be separated from the school because they have not fulfilled this requirement. A legal receipt must be provided for all payments made.

4/ According to the Directive issued by the Ministry, a student who is not an Ethiopian citizen may be required to pay tuition fees at government educational institutions. However, migrant children who have received permission to live in Ethiopia have the right to attend general education free of charge according to the Directives issued by the Ministry.

https://ethiodata.et/

፭/ መንግሥታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ለሚደረግ የትምህርትና ሌሎች ተጓዳኝ ክፍያዎች ሁሉ ሕጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡

## ፲፭. የግዴታ ትምህርት መግቢያ ዕድሜ

፩/ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከአራት አመት እስከ ስድስት አመት እድሜ ያላቸውን ሕፃናት የሚያጠቃልል ሲሆን የቅድመ አንደኛ ደረጃ የግዴታ ትምህርት የመግቢያ እድሜ አምስት አመት ይሆናል፡፡ እድሜያቸው አራት አመት የሞላቸው ሕፃናት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በሌሎች አማራጮች እንዲማሩ ይደረጋል፡፡

፪/ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መግቢያ ዕድሜ ሰባት ዓመት ነው፡፡ የዕድሜ አቆጣጠሩም ከተመዘገቡበት ዓመት መስከረም ወር በፊት በነበረው ዓመት ሰባት ዓመት የሞላቸውንና በተመዘገቡበት ዓመት እስከ የካቲት ፴ ቀን ድረስ ሰባት ዓመት የሚሞላቸውን ይጨምራል፡፡

፫/ በመደበኛው ዕድሜ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት መላክ አስቸጋሪ በሚሆንባቸው የገጠርና የአርብቶ አደር አካባቢዎች ወይም በሌሎች አጥጋቢ ምክንያቶች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ልጆችን ትምህርት ቤት ማስገባት ካልቻሉ የትምህርት ቤት መግቢያ ዕድሜው እስከ አሥራ ሁለት ዓመት ከፍ ሊል ይችላል፡፡

፬/ ከ፯-፲፪ አመት የሆናቸው ሕፃናት በተለያዩ ምክንያቶች የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ባይከታተሉም አንደኛ ክፍል ገብተው እንዲማሩ ይደረጋል፡፡

5/ Legal receipts must be issued for all tuition and other related fees paid by non-governmental schools.

## 15. Age of Entry into Compulsory Education

1/ Pre-primary education includes children between the ages of four and six years, and the entry age for compulsory pre-primary education is five years. Pre-primary education for four-year-old children will be offered through other options.

2/ The entry age for primary education is seven years. The age limit includes those who have turned seven years old in September of the year before the year of registration and those who will turn seven years old by February 28 or 29th of the year of registration.

3/ In rural and pastoral areas where it is difficult to send students to school at the regular age, or for other satisfactory reasons if parents or guardians are unable to send children to school before this proclamation goes into effect, the school entry age may be raised to twelve years.

4/ Even if children aged 7-12 years do not attend pre-primary education for various reasons, they will be allowed to enter the first grade.

https://ethiodata.et/

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ቢኖርም ዕድሜያቸው ከ፲፪-፲፬ አመት የሆናቸው ሕፃናት በተፋጠነ የትምህርት መርሃ ግብር እንዲሳተፉ በማድረግ ወደ መደበኛው ወይም ወደ የጐልማሶች ትምህርት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

፮/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ትምህርቱን በመከታተል ላይ የሚገኘው ተማሪ በሚሳየው ብቃት መሰረት ወደ መደበኛ መርሃ ግብር ተማሪነት ተዛውሮ ሊማር ይችላል፡፡

## ፲፮. የትምህርት ቤት መግቢያ ዕድሜ ማረጋገጫ

፩/ የልደት የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው አካል በሚሰጥባቸው አካባቢዎች የትምህርት መግቢያ ዕድሜ በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ይረጋገጣል፡፡

፪/ በሌሎች ሁኔታዎች የተማሪው የትምህርት ቤት መግቢያ ዕድሜ በወላጁ ወይም በአሳዳጊው በሚሰጥ የቃል መሐላ ማረጋገጫ ይታወቃል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው የዕድሜ ማረጋገጫ ህጻኑ በህጉ የተመለከተውን እድሜ አለማሟላቱ በግልጽ እስካልተረጋገጠ ድረስ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ምክንያት ማንኛውም ሕጻን የትምህርት ዕድል ሊነፈግ አይችልም፡፡

## ፲፯. ተማሪዎችን በመንግሥት ትምህርት ቤት ስለመቀበል

፩/ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን አንድ የመንግሥት የትምህርት ተቋም ኢትዮጵያዊ ወይንም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፍቃድ ያገኘ ስደተኛ ሕጻን ትምህርት እንዳያገኝ መከልከል አይችልም፡፡

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of this Article, children aged 12-14 years old will be allowed to participate in an accelerated education program so that they can be transferred to regular or adult education.

6/ Subject to Sub-Article (5) of the same Article, according to the Directive issued by the minister, a student attending the adult education and training program may be transferred to a regular program based on their ability.

## 16. Proof of School Entry Age

1/ In areas where birth certificates are issued by the appropriate body, the age of school entry is verified by the certificate issued.

2/ In other cases, the school entry age of the student is ascertained by an affidavit from the parent or guardian.

3/ No child can be denied an education opportunity on the grounds that proof of age specified in this Article has not been provided unless it is clearly proven that the child does not meet the age specified by the law.

## 17. Admitting Students to Government Schools

1/ A government educational institution cannot prevent an Ethiopian or immigrant child who has been granted permission to live in Ethiopia from getting an education.

https://ethiodata.et/

፪/ በሁሉም ደረጃ ትምህርት እንዲሰጥ የተቋቋመ የመንግሥት የትምህርት ተቋም ትምህርት ቤት ለመግባት ጥያቄ በሚያቀርብ ሕጻን፣ በወላጆቹ ወይም በአሳዳጊዎቹ ላይ የተለየ ማጣሪያ ማድረግ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ወጣት ጥፋተኛ መሆኑን የወሰነው ፍርድ ቤት አጥፊው ወደ ትምህር ቤት እንዳይገባ በሰጠው ውሳኔ በግልጽ እስካልከለከለ ድረስ ማንኛውም የትምህርት ተቋም ተማሪው ትምህርት ቤት እንዳይገባ ወይም ከትምህርት ቤት እንዲባረር ማድረግ አይቻልም፡፡

፬/ ወጣት ጥፋተኛውም የእርማት ጊዜውን ከጨረሰ በኋላ ወደትምህርት ቤት የመግባት መብት አለው፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተደነገገው አኳኋን አንድ ተማሪ ከነበረበት ትምህርት ቤት ወደሌላ ትምህርት ቤት መዛወር ሲያስፈልገው ጥያቄው የቀረበለት ትምህርት ቤት ተማሪውን የመቀበልና ዝውውሩ የሚጠይቀውን አስፈላጊውን መረጃ ማቅረቡን አረጋግጦ የመቀበል ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

## ፲፰. የወላጆችና የአሳዳጊዎች ግዴታና ኃላፊነት

ወላጆችና አሳዳጊዎች የሚከተሉት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች አለባቸው:-

፩/ በህመም፣ በትምህርት ተቋማት አለመኖር ወይም እጥረትና ከአካባቢ በመፈናቀል ችግር ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ልጁ ወይም የሚያስተዳድረው ልጅ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት እንዲከታተል የማድረግ፣

2/ A Government educational institution established to provide education at all levels shall not impose special screening on a child, his parents or guardians who makes a request for admission to a school.

3/ Subject to the provisions of Sub Article 3 of Article 92 of this proclamation, any educational institution cannot prevent the student from entering school or expel them from school unless the court judge who has decided that the youth is guilty clearly prohibits them from entering school.

4/ The juvenile offender has the right to go to school after completing their correctional period.

5/ When a student needs to transfer from their school to another school in accordance with Article 13 Sub-Article 4 of this Proclamation, the school to which the request was submitted has the duty and responsibility to accept the student shall ensure that all necessary information has been provided.

## 18. Duties and Responsibilities of Parents and Guardians

Parents and guardians have the following duties and responsibilities:

1/ Any parent or guardian whose child is in pre-primary level, except for illness, absence or shortage of educational institutions, and displacement from the area, is obliged to attend primary and middle-level education;

https://ethiodata.et/

፪/ ልጆቻቸው ትምህርት እንዲያቋርጡ ከማድረግ በተለይም ልጆችን ያለዕድሜ ጋብቻ እንዲፈጽሙ ከማስገደድ ወይም ከመገፋፋት መታቀብ፤

፫/ የልጆቻቸውን ደህንነትና ትምህርት በተመለከተ ከትምህርት ቤቶች አስተዳደር ጋር የመተባበር፣ ለትምህርት ተቋማቱ ደንቦችና መመሪያዎች የመገዛት፤

**፲፱. የመንግሥት ትምህርት ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

፩/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፤ በአንደኛ ደረጃና በመካከለኛ ደረጃ ያለ ትምህርት ቤት የግዴታ ትምህርት ዕድሜ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያለማቋረጥ መከታተላቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን በተለይም ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን የማከናወን ኃላፊነት አለበት:-

(ሀ) አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት የቀረበት ምክንያት እንዲጣራ ማድረግ፣

(ለ) ተማሪው ከትምህርት የቀረበትን ምክንያት እንዲገልጹ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ደብዳቤ መጻፍ፣

(ሐ) ተጣርቶ በተገኘው ውጤት መሠረት ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች ጋር በመመካከር ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

(መ) ይህንኑ በተመለከተ ለትምህርት ቤቱ የበላይ አመራር ወይም ለሚቀጥለው የበላይ አካል ዘገባ ማቅረብ፣

2/ Parents and guardians should refrain from forcing their children to drop out of school, especially from forcing or pushing them into early marriage;

3/ Regarding the safety and education of their children, parents and guardians are obliged to cooperate with the school management and obey the rules and regulations of the educational institutions;

**19. Duties and Responsibilities of Government Schools**

1/ Pre-primary, primary, and middle-level schools are obligated to ensure that students of compulsory school age attend school regularly.

2/ In particular, schools are responsible for the following actions:

a) Investigating the reasons for a student's absence,

b) Sending a letter to parents or guardians to explain the reason for the student's absence,

c) Taking appropriate corrective action in consultation with parents or guardians if there is an issue,

d) Submitting a report regarding the same to the school management or the next higher authority,

https://ethiodata.et/

## ፳. የመንግሥት አካላት ተግባርና ኃላፊነት

፩/ ነጻና የግዴታ ትምህርትን በማረጋገጥ ረገድ መንግሥት የሚከተሉትን ኃላፊነቶች ይወጣል፡፡

(ሀ) ዕድሜያቸው ለግዴታ ትምህርት የደረሱ ሕጻናት ሁሉ ትምህርት ቤት መግባታቸውንና ትምህርታቸውን እየተከታተሉ መሆኑን የማረጋገጥ፣

(ለ) የተለየ ድጋፍ በሚፈልጉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙ ሕጻናት፣ ለአደጋ የተጋለጡ ወይም ተፈላጊውን ዕድል ያላገኙ ሕጻናት ከማንኛውም መድሏዊ አሠራር ነጻ ሆነው አጠቃላይ ትምህርት እየተከታተሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

(ሐ) ግልጽ በሆነ ደንብና ሥርዓት መሠረት ለትምህርቱ የሚያስፈልጉትን መምህራንና ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የመመደብ፣

(መ) ትምህርት ቤቶችን መገንባት፣ የመማሪያና የማስተማሪያ ቁሳቁስ ማቅረብና አስፈላጊውን በጀት የመመደብ፣

(ሠ) የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ከወጣው የትምህርት ጥራት ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የማረጋገጥ፣

(ረ) ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ላላቸው ወይም አካላዊ ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ የተለየ ትምህርት ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣

(ሰ) እያንዳንዱ ተማሪ በግዴታ ትምህርት መርሐ ግብር መካተቱን፣ ትምህርቱን መከታተሉንና በአግባቡ መጨረሱን የማረጋገጥ፣

(ሸ) ሕጻናት የግዴታ ትምህርታቸውን መፈጸም እንዲችሉ ተገቢውን ማበረታቻ መስጠት፣

## 20. Duties and Responsibilities of Government Bodies

1/ The Government shall discharge the following responsibilities in ensuring free and compulsory education.

a) Ensuring that all children of compulsory school age attend school,

b) Ensuring that children in need of special support, at risk, or without desired opportunities attend general education free from any discrimination,

c) Deploying/assigning teachers and other support staff as needed according to clear rules and Regulations,

d) Building schools, providing learning and teaching materials, and allocating the necessary budget,

e) Ensuring that the education provided meets quality standards,

f) Facilitating the provision of special education based on the needs of students with special talents or physical disabilities,

g) Ensuring that every student is included in the compulsory education program, attends, and completes the education properly,

h) Providing appropriate incentives for children to complete their compulsory education,

https://ethiodata.et/

(ቀ) ትምህርት ቤቶች በአግባቡ ሥራዎቻቸውን እያከናወኑ መሆናቸውን የመቆጣጠር፣

(በ) እስከ ዝቅተኛው የመንግሥት አስተዳደር ዕርከን በሚገኙ አካባቢዎች በመውረድ ዕድሜያቸው ለግዴታ ትምህርት የደረሱ ተማሪዎችን መዝግቦ የመያዝ።

፪/ የዚህን አንቀጽ አተገባበር በተመለከተ ሚኒስቴሩ አግባብ ያላቸው አካላት የሚኖርባቸውን ግዴታ የሚያመለክት መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአጠቃላይ ትምህርት አደረጃጀት

### ፳፩. ልዩ ልዩ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት

፩/ በዚህ አዋጅ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት:-

(ሀ) የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፣

(ለ) የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣

(ሐ) የግል ትምህርት ቤቶች፣

(መ) በሲቪል ማኅበራት የሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች፣

(ሠ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የወጭ ሀገራት ማኅበረሰቦች ትምህርት ቤቶች፣

(ረ) በውጭ ሀገራት ባሉ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች፣

(ሰ) ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች፣

(ሸ) በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች፤ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች አካላት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶችን ይጨምራሉ፡፡

፪/ የማረሚያ ተቋማት አጠቃላይ ትምህርት መስጠት የሚችሉ ትምህርት ቤቶችን መክፈት ስለሚችሉበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

i) Monitoring that schools are performing their duties properly,

j) Registering students who have reached the age of compulsory education in areas at the lowest level of government administration.

2/ The Ministry will issue Directives indicating the obligations of relevant parties regarding the implementation of this article.

## Part Three

## Organization of General Education

### 21. Various Institutions of General Education

1/ Institutions of general education, as defined by this proclamation, include:

a) Government schools ,

b) Public schools,

c) Private schools,

d) Schools run by civil societies,

e) Schools for foreign communities living in Ethiopia,

f) Ethiopian community schools in foreign countries,

g) International schools,

h) Schools owned by religious institutions ፤or scholes which regulated by other institutions according to the Directive issued by the Ministery.

2/ The Ministry will issue Directives on the conditions under which Prison administration institutions can open schools that provide general education.

https://ethiodata.et/

፫/ አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች መደበኛ የሆኑ፣ መደበኛ ያልሆኑ፣ የጐልማሶች ወይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ትምህርት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ለ) ላይ የተጠቀሰው የሕዝብ ትምህርት ቤትን አደረጃጀትና አመራርን በተመለከተ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፪. <u>የትምህርት ተቋም ሊያሟላቸው የሚገባቸው መስፈርቶች</u>**

፩/ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

(ሀ) የትምህርት ቤቱን የአስተዳደርና የሥራ አመራር አካላት፣ መምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን የሚያመለክት ድርጅታዊ መዋቅር፤

(ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ስታንዳርድ በሚገለጸው መሠረት ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ የተማሪዎች ቁጥር፤

(ሐ) ለአደጋ ያልተጋለጠ፣ የአደጋ መከላከያ እና መውጫዎች ያሟላ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራን እና በሠራተኞች ላይ ጾታዊና አካላዊ ጥቃት ለመፈጸም ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ ሁኔታዎች የጸዳ አካባቢ፤

(መ) የመማሪያ ክፍሎች፣ የአገልግሎት መስጫ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና አግባብ ባለው አካል በሚወጣ የደረጃ መስፈርት መሠረት የተሟሉ የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁስ፤

3/ Schools providing general education may be formal, non-formal, adult, or special education schools.

4/ The details regarding the organization and leadership of a public school, as referred to in letter (b) of Sub Article (1) of this Article, shall be determined by the Directive issued by the Ministry.

**22. <u>Requirements for Educational Institutions</u>**

1/ Each school must ensure it meets the following conditions.

a) An organizational structure that includes the school's administrative and management bodies, teachers, and support staff;

b) The minimum number of students as defined by the standards issued pursuant to this Proclamation;

c) An environment that is safe, equipped with emergency exits, and free from conditions conducive to sexual and physical abuse of students, teachers, and staff;

d) Classrooms, service facilities, gymnasium facilities, and educational equipment and materials that meet the standards issued by the appropriate body;

https://ethiodata.et/

(ሠ) ለመምህራን አገልግሎት የሚውሉ ጽሕፈት ቤቶችና የመሰብሰቢያ ክፍሎች፤

(ረ) ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ-መጻሕፍትና የተግባር ትምህርት መስጫ ቤተ ሙከራዎችና የትምህርት ማበልፀሚያ ማዕከላት፤

(ሰ) የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመደገፍ የሚያስችል አስፈላጊው በጀት፤

(ሸ) ከአዋኪ ሁኔታዎች የፀዳ እና ምቹ የመማሪያ አካባቢ፤

(ቀ) ደረጃቸውን የጠበቁና ንጽሕናቸው የተሟላ፣ ጽዱ፣ ምቹ ንጽሕና መጠበቂያ ክፍሎች እና ውሃ፤

(በ) ልዩ ፍላጐት ላላቸው አካታችና ተደራሽ እንዲሆን ማስቻል፤

፪/ ሚኒስቴሩ አንድ ትምህርት ቤት ሊያሟላ የሚገባውን ተጨማሪ መስፈርት አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፳፫. የትምህርት ተቋም ተግባርና ኃላፊነት

አንድ የትምህር ተቋም የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

፩/ በዚህ አዋጅ እንዲሁም፣ በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችለው ራሱን የቻለ የአስተዳደር መዋቅር የመዘርጋት፣

፪/ የሰው፣ የቁስና የገንዘብ ሀብቱን በአግባቡ የማስተዳደር፣

፫/ የትምህርት ሥራውን ክንዋኔ በተቀመጡለት ስታንዳርዶች መሠረት የማደራጀት፣

e) Offices and meeting rooms for teachers;

f) Regional-of-the-art libraries, flexile teaching laboratories, and pedagogical enrichment centers;

g) The necessary budget to support the teaching and learning process;

h) A conducive and comfortable learning environment free of distractions;

i) Standard, hygienic, complete, clean, comfortable, and inclusive restrooms and water facilities;

j) Enabling it to be convenient and suitable as well as accessible for citizens with special needs;

2/ The Minister or their representative may issue detaile Directive regarding additional requirements that a school must meet.

## 23. Duties and Responsibilities of Educational Institutions

An educational institution has the following duties and responsibilities:

1/ Establishing an independent administrative structure that enables the work to be carried out by this proclamation and the Directives and regulations issued pursuant to it,

2/ Properly managing human, material, and financial resources,

3/ Organizing the performance of educational activity according to set standards,

https://ethiodata.et/

፬/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የተማሪዎችን መብትና ግዴታ ባከበረ መልኩ ተማሪዎችን ተቀብሎ የማስተማር፣

፭/ እንደየትምህርት ደረጃው ሥራውን በፀደቀ ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የማካሄድ፣

፮/ ፈተናዎችን የማውጣት፣ የማስተዳደርና ለተፈታኙ ተገቢውን የውጤት ማረጋገጫ የመስጠት፣

፯/ በሚቀመጡ ስታንዳርዶች መሠረት ተማሪዎች ከአንድ የትምህርት ደረጃ ወደቀጣዩ ማለፋቸውን የመወሰን፣

፰/ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጃቸው ስታንዳርዶች መሠረት ደረጃቸውን የማሻሻል፣

፱/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በማድረግ የሚቀጠሩት መምህራን አነስተኛውን መመዘኛ ያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

፲/ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሥነ ሥርዓት የማስከበርና ምቹ የትምህርት ሁኔታ መኖሩን የማረጋገጥ፣

፲፩/ ወላጆች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

፲፪/ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎች የመፈጸምና የማስፈጸም፣

፲፫/ እየተሰጡ ያሉት ትምህርቶች ጥራትና አግባብነት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ከፀደቁ ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

፲፬/ የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የሌሎችንም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሆኑ አካላትን መብቶችና ጥቅሞች የማስጠበቅ፣

4/ Receiving and teaching students in a manner that respects their rights and obligations as per this proclamation,

5/ Carrying out work according to the approved national or regional curriculum based on the level of education,

6/ Developing exams, managing them, and providing the examinee with the appropriate certificate of results,

7/ Determining whether students have passed from one level of education to the next according to established standards,

8/ Improving their standards according to the standards set by the Ministry,

9/ Ensuring that hired teachers meet the minimum standards based on the standards issued by the Ministry,

10 / Maintaining order on the school premises and ensuring a comfortable learning environment,

11/ Facilitating conditions for parents to actively participate in the learning process,

12/ Enforcing this proclamation and the rules and regulations issued pursuant to it,

13/ Ensuring the quality and relevance of the lessons taught align with nationally or regionally approved policies and directives,

14/ Protecting the rights and interests of students, teachers, and others involved in the learning and teaching process,

https://ethiodata.et/

፲፭/ ተማሪዎች በተጓዳኝ ትምህርት በብቃት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የመፍጠር፣

፲፮/ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የመቆጣጠር ስልጣን ለተሰጠው መንግስታዊ አካል የቁጥጥር ሥራዎች ሲካሄዱ የማገዝና የመተባበር፣

፲፯/ ስለሥራ እንቅስቃሴው ለሚመለከተው የትምህርት አስተዳደር አካል ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ፣

፲፰/ የትምህርት ማኅበረሰቡን ተቋማዊ ተሳትፎ ትርጉም ባለው መልኩ የማጠናከር፣

፲፱/ አግባብ ያላቸው የመንግሥት አካላት የሚሰጡትን ሕጋዊ ተግባሮች ማከናወን እንዲሁም ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ማከናወን፣

**ክፍል አራት**

**ሥርዓተ ትምህርት**

**፳፬. የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት መርሆዎችና ደረጃዎች**

፩/ ተማሪዎች ሁለንተናዊ ሰብዕና ተላብሰው በትምህርቱ ሂደት እንዲያልፉ የሚያደርግ፣ ጉዳዮችን በጥልቀት የሚመረምር፣ የትምህርት አሰጣጡን ምዘና ዘዴና አካሂድ ከግምት የሚያስገባ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችንና ዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎችን አጣጥሞ የሚያካትት፣ ገንቢ፣ ችግር ፈቺና የተቀናጀ አሠራር ማስፈንን የሚጠይቅ ሥርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል።

15/ Creating an environment where students can effectively participate in co-curricular activities,

16/ Assisting and cooperating with the government body authorized to carry out control activities according to the relevant law,

17/ Submitting current reports to the next education management body about work activities according to given instructions,

18/ Strengthening the institutional participation of the educational community in a meaningful way,

19/ Carrying out legal duties assigned by relevant government bodies and other related tasks,

**Part Four**

**Curriculum**

**24. Principles and Standards of Curriculum Devlopment**

1/ A curriculum will be developed to allow students to progress through the education process as well-rounded individuals, examining issues in depth, considering teaching and assessment methods, including indigenous knowledge and global situations, and establishing a constructive, problem-solving, and integrated system.

https://ethiodata.et/

፪/ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ቀረጻ በሚካሄድበት ጊዜ የፌደራል መንግስትና ክልሎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት ሁሉ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

(ሀ) ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ፣ በአካቶ ትምህርት ላይ የተመሠረተና ተግባር ተኮር የሆነ፣

(ለ) አግባብነት ያለው፣ ችግር ፈቺና በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ፣

(ሐ) ከኅብረተሰቡ የቀን ተቀን ኑሮ ጋር የተዛመደና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ከግምት ያስገባ፣

(መ) ተማሪዎች ተፈላጊውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ የሚያበቃ፣ ድግግሞሽን የሚያስቀርና ወደ ሚቀጥለው የትምህርት ዕርከን ለመሸጋገር የሚያስችላቸው እየዳበረ የሚሄድ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን የሚከተል፣

(ሠ) ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ባሉት ዕርከኖች በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጥ ትምህርትን ዓላማ ያደረገ፤ ትምህርቱን ከሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ከተማሪዎች ግላዊና ማኅበራዊ ሕይወት ጋር ያገናዘበ፣

(ረ) ትምህርት ቤቶች ትምህርቱን በተማሪው ዙሪያ ካሉ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ ለመስጠት እንዲችሉ የሚያደርግ፣

(ሰ) ሥነ ምግባርና ግብረ ገብነትን፣ የሀገር ፍቅር ስሜትን፣ ሥራ መውደድንና ሥራ ፈጠራን፣ አዎንታዊ አመለካከትን፣ ሰብዓዊ መብትን እንዲሁም፣ ባህልን፣ ቅርስን፤ ተፈጥሮንና አካባቢን መንከባከብንና ማድነቅን የሚያበረታታ፣

2/ The federal government, regional administrations, and all other relevant institutions should consider the following elements during curriculum design and development.

a) Student centered, inclusive educati on-based, and practice-oriented,

b) Relevant, problem-solving, and research-based,

c) Considering Indigenous knowledge related to the daily life of society,

d) Following an evolving teaching method that enables students to acquire the required knowledge and skills, avoid repetition, and progress to the next level of education,

e) Aimed at mother tongue education from pre-primary to intermediate levels, considering national and international contexts and the personal and social life of students,

f) Enabling adaptation to local conditions around the student;

g) Encouraging patriotism,entreprene urship, ethics and moral, positive attitudes, human rights, culture, heritage, and appreciation of nature and the environment,

https://ethiodata.et/

(ሸ) የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጥ ፣

(ቀ) ለሴት እና ወንድ ተማሪዎች እኩል ትኩረት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት ሥራዎች በፌደራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መጻሕፍት ተቀባይነት ባገኙ የትምህርት አሰጣጥ መርሆዎች መሠረት መዘጋጀታቸውንና አካባቢያዊ፣ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ባረጋገጠ መልኩ መከናወን አለባቸው፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስፈልጉ መጻሕፍት ዝግጅት፣ ኅትመትና ሥርጭት ያከናወናል፡፡

፭/ አግባብ ያላቸው የክልል የትምህርት አካላት የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃና የጐልማሶች ትምህርትና ሥልጠና መማሪያ የማስተማሪያ መጻሕፍትን የማዘጋጀት፣ የማሳተምና የማሰራጨት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፮/ ሚኒስቴሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግበው ሥራቸውን የሚያካሒዱ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶችና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች የሚገለገሉባቸውን ሥርዓተ ትምህርት ያፀድቃል፡፡

፯/ የውጪ ሀገር ማህበረሰብ ትምህርት ቤቶችና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች የሚተገብሯቸው ሥርዓተ ትምህርቶች የሀገራችንን እሴቶች የማይቃረኑ መሆናቸውን ትምህርት ሚኒስቴር ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፡፡

h) Providing basic knowledge and skills in science and technology,

i) It should be equally attentive to female and male students.

3/ Curriculum design and preparation should ensure that textbooks prepared at the federal and regional levels adhere to accepted teaching principles and meet local, national, and international standards.

4/ The Ministry prepares, publishes, and distributes books for middle leevel education.

5/ Appropriate regional education bodies are responsible for preparing, publishing, and distributing textbooks for pre-primary, primary, middle level, and adult education and training.

6/ The Ministry approves the curriculum used by foreign community schools and international schools registered and operating in Ethiopia.

7/ The Minister shall be responsible for ensuring that the curricula implemented by foreign community schools and international schools do not contradict the values of the country.

https://ethiodata.et/

**፳፭. የሥርዓተ ትምህርት አጠቃላይ አቅጣጫዎች**

፩/ አጠቃላይ ትምህርት ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው የክልል አካላት፣ ከመምህራን፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርብ በመመካከር በሚያወጣው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

፪/ የክልል አካላት በየዕርከኑ ለሚገኙ የትምህርት ደረጃዎች ሥርዓተ ትምህርት የሚቀርጹበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፮. የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ይዘትና አተገባበር**

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በሚኒስቴሩ የሚዘጋጅ ሲሆን ትምህርቱ የሚመለከታቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነትና የሚሰጥበትን የትምህርት ዕርከን የሚያመላክት ይሆናል፡፡

፪/ ሥርዓተ ትምህርት የሚከተሉትን ይዘቶችና አደረጃጀቶች ያካትታል፡፡

(ሀ) የአጠቃላይ ትምህርቱ መርሐ ግብር ዓላማዎች፣

(ለ) የአጠቃላይ ትምህርት ዓይነቶች ደረጃ፣

(ሐ) በመርሐ ግብሩ የሚሸፈኑ የትምህርት ዓይነቶች፣

(መ) ተማሪዎች በግዴታ እና በአማራጭ ሊወሰዷቸው የሚገቡ የትምህርት ዓይነቶችና የሚያልፉባቸው መርሐ ግብሮች እና

(ሠ) ተማሪዎች ትምህርቱን በሚገባ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚሰጡ ፈተናዎችን የሚመለከቱ ደንቦችና ሥርዓቶች፡፡

**25. General Directions of Curriculum**

1/ General education will be based on the curriculum framework issued by the Ministry in close consultation with relevant regional bodies, teachers, higher education institutions, and other relevant entities.

2/ The conditions under which regional bodies design the curriculum for each level of education will be determined by directives issued by the Ministry.

**26. Curriculum Framework Content and Implementation**

1/ The Ministry shall prepare the general education curriculum framework and will specify relevant sections of society, as well as the type and level of education.

2/ Curriculum organization and content will include the following.

a) Objectives of the general education curriculum,

b) Levels and types of general education,

c) Subjects covered in the schedule,

d) Compulsory and optional subjects and programs students must take,

e) Rules and regulations regarding examinations given to ensure students have successfully completed the course.

https://ethiodata.et/

፫/ በሚኒስቴሩ ተቀርጾ የሚዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ አጠቃላይ ትምህርት በሚሰጡ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

፬/ በክልሎች የሚዘጋጁ የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት በሀገር አቀፍ በተዘጋጁት የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ እና መርሃ- ትምህርቶች መሠረት መሆኑን በሚኒስቴሩ ይረጋገጣል፡፡

፭/ ክልሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ እና መርሃ- ትምህርቶች መሠረት የቅድመ አንደኛ ደረጃ፤ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና የጐልማሶች ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

## ፳፯. የአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት አግባብነት

፩/ በሥርዓተ ትምህርት የሚሸፈኑ የትምህርት ዓይነቶች በይዘታቸው ዓለማቀፋዊ፣ አግባብነት ያላቸውና በሀገሪቱ ልዩ ፍላጐት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

፪/ በየዕርከኑ ለሚሰጡ ትምህርቶች የሚቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች የሚፈለገውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲያበለጽጉ በሚያስችልና ከአንድ መልካም ዜጋ የሚጠበቀውን ማኅበራዊና ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ ሊያበቃቸው በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

3/ The curriculum framework designed and developed by the Ministry should be implemented by all regional administrations and city administrations that provide general education.

4/ The Minister will confirm that textbooks prepared by the regions align with the nationally prepared curriculum framework and syllabuses.

5/ Pre-primary, primary, middle, and adult education and training curricula should be developed by the study, based on the curriculum framework and programs prepared by the regions at the national level.

## 27. Relevance of General Education Curriculum

1/ The subjects included In the general education curriculum should be universal in contents, should be universal relevant and relevant, and based on the specific needs of the country.

2/ The curriculum designed for lessons at each level should enable students to develop the required knowledge, skills, and attitudes, and fulfill the social and national responsibilities expected of good citizens.

https://ethiodata.et/

**፳፰. <u>የማስተማሪያ ቋንቋ</u>**

፩/ የአፍ-መፍቻ ቋንቋ እንደትምህርት ዓይነትነት እና እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ የሚሰጥ ሆኖ እንደትምህርት ዓይነትነት እና እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነት መሰጠቱ የሚያበቃበት የክፍል ደረጃ በክልሎች ተወስኖ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

፪/ የእንግሊዘኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ቋንቋነት ሥራ ላይ መዋል የሚጀምርበት በክልሎች የሚወሰን ሆኖ በአስገዳጅነት ከ፱ኛ ክፍል ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል፤ ስለአፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ትምህርቱ በምልክት ቋንቋ ይሰጣል፡፡

፬/ ለዓይነ ስውራን ተማሪዎች ትምህርቱ በብሬል ወይም በተስማሚ ቴክኖሎጂ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

**፳፱. <u>ሌሎች ቋንቋዎችን ስለማስተማር</u>**

፩/ ተማሪዎች ቢያንስ ሦስት ቋንቋዎችን እንዲማሩ ይደረጋል፤ ስለአፈጻጸሙ ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች ይወሰናል።

፪/ አንድ ተጨማሪ የሀገር ውስጥ ቋንቋ በሕገ መንግሥቱ ሲረጋገጥ ከፌደራል የሥራ ቋንቋዎች መካከል የተማሪ ወይም የወላጅ ምርጫን ታሳቢ በማድረግ በየደረጃ ባለው የትምህርት መዋቅር ተወስኖ እንደ አንድ ትምህርት ዓይነት ከ፫ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ፲ኛ ክፍል የሚሰጥ ይሆናል፡፡

፫/ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል፡፡

**28. <u>Language of Instruction</u>**

1/ The mother tongue is taught as a form of subject and medium of instruction from pre-primary level, with the class level at which it ends as a form of education and as a language of instruction determined and implemented by the regions.

2/ The English language will be used as the medium of instruction, depending on the region, and will be implemented compulsorily from the 9th grade. The Ministry may issue detailed Directive for its implementation.

3/ Teaching for deaf students shall be conducted in sign language.

4/ For blind students, subjects shall be made available in Braille or through appropriate adaptive technology.

**29. <u>Teaching Other Languages</u>**

1/ Students will be taught at least three languages, as determined by the laws issued by the regional governments and city administrations regarding implementation.

2/ When an additional local language is constitutionally recognized, student or parent preferences among the federal working languages shall be considered. The language will be incorporated into the educational structure at all levels as a subject, from grade 3 to grade 10.

3/ The English language will be taught as a subject from pre-primary level upwards.

https://ethiodata.et/

፬/ ባላቸው ልዩ ፍላጎት ምክንያት በምልክት ቋንቋ፣ በብሬል ቋንቋ መማር ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ትምህርቱ ስለሚሠጥባቸው ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

፭/ አንድ ተጨማሪ የውጭ ቋንቋ ክልሉ በሚመርጠው መሠረት ከ፱ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ፲ኛ ክፍል በአማራጭነት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## ፴. <u>አንኳርና መሠረታዊ ትምህርቶች</u>

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ አንኳርና መሠረታዊ ትምህርቶችን ያካተተ ይሆናል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ አንኳርና መሠረታዊ ትምህርቶችን የትኞቹ እንደሆኑ በየደረጃው የሚሠጡበትን አኳኋን የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ የግብረገብነት ትምህርት በአንደኛ ደረጃ በመሠረታዊ ትምህርትነት፣ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከዜግነት ትምህርት ጋር ተካትቶ ይሰጣል፡፡

፬/ ለሥርዓተ ትምህርቱ ከተመደበው የትምህርት ጊዜ ውስጥ የአንኳርና የመሠረታዊ ትምህርቶች ምጣኔ መቶኛ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

፭/ ለእያንዳንዱ አንኳርና መሠረታዊ ትምህርት የሚመደበው ጊዜና የሚሰጠው ክብደት በሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ይገለጻል፡፡

፮/ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ የሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ሥርዓተ-ትምህርት ሚኒስቴሩ የሚያዘጋጀውን ማዕቀፍ እና መርሃ-ትምህርቶች መሠረት በማድረግ በክልሎች ይቀረጻል፡፡

4/ Due to the special needs of students, the Ministry shall issue a Directive on the conditions under which the subject is taught to students who require instruction in both sign language and the Brail language.

5/ An additional foreign language shall be offered as an elective from grade 9 to grade 10, as selected by the region.

## 30. <u>Core and Basic Lessons</u>

1/ The general education curriculum framework will include core and basic subjects.

2/ The Ministry will issue detailed Directives on how core and basic subjects are taught at each level.

3/ Ethical education will be included as a basic subject at the primary level and integrated with citizenship education at the middle and high school levels.

4/ The percentage of core and basic subjects in the academic period allocated for the curriculum is determined by the Ministry.

5/ The time and weightage allocated to each core and basic subject are defined in the curriculum framework.

6/ The pre-primary, primary, and middle-level curricula for all subjects will be designed by regional bodies based on the framework and syllabus developed by the Ministry.

https://ethiodata.et/

**፴፩. ተጓዳኝ ትምህርቶች**

፩/ ሁሉም አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ተጓዳኝ ትምህርትን አስመልክቶ በሚኒስቴሩ የሚቀርጸውን የሥርዓት ትምህርት ማዕቀፍ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ ተማሪዎች በተጓዳኝ ትምህርቶች የሚሳተፉት በሚመርጡት ዘርፍ ሲሆን አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት ዘመን ቢያንስ በአንድ ተጓዳኝ የትምህርት ዓይነት መሳተፍ አለበት፡፡

፫/ ተጓዳኝ ትምህርቶች በትምህርት ቤቶች ዓመታዊ ዕቅዶች ውስጥ እየተካተቱና ግልጽና የታወቀ በሆነ መለኪያ እየተመዘኑ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

**፴፪. የአጠቃላይ ትምህርት የትምህርት ምጣኔ**

፩/ ለአንድ ተማሪ የሚሰጠው የትምህርት ምጣኔ ተማሪው ለእረፍት፣ ለመዝናናት፣ ለግል ፍላጎት የሚያስፈልገው ጊዜ ለትምህርቱ ከተመደበለት ጊዜ ጋር እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት ለመመላለስ የሚፈጅበት ጊዜና የቤት ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ጊዜ በታሳቢነት ተወስዶ የሚወስን ይሆናል፡፡

፪/ ዕለታዊና ሳምንታዊ የትምህርት ጊዜያትና ተማሪዎች ወደክፍል የሚገቡበትንና ከክፍል የሚወጡበት ሰዓት አግባብ ባለው የክልል ወይም የአካባቢ የትምህርት አስተዳደር አካል ይወሰናል፡፡

፫/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት በየዕለቱ እና በየሳምንቱ የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ዝቅተኛና ከፍተኛ ቁጥር በሚኒስቴሩ በሚወጣ ስታንዳርድ ይወሰናል፡፡

**31. Co-curricular activities**

1/ All general education institutions are responsible for implementing the curriculum framework formulated by the Ministry regarding complementary education.

2/ Students must participate in at least one co-curricular activity each academic year, and they are encouraged to choose activities that interest them.

3/ Co-curricular activities must be included in the annual plans of schools and implemented with clear and well-defined standards.

**32. Education Rate**

1/ The amount of education provided to a student in general education will take into consideration the time needed for rest, recreation, personal needs, lessons, travel to school, and homework.

2/ The daily and weekly schedules, including the times students enter and leave classrooms, are determined by the relevant regional or local education management body.

3/ For pre-primary, primary, middle, and secondary level education institutions, the minimum and maximum number of subjects offered daily and weekly is determined by standards issued by the Ministry.

https://ethiodata.et/

**፴፫. የትምህርት ዓመታዊ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ**

፩/ እንደየአየር ንብረት፣ የወላጆች የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮችን በመሳሰሉ ምክንያቶች ክልሎችና አንዳንድ አካባቢዎች ከሀገር አቀፉ የተለየ የትምህርት ዓመታዊ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ በመደበኛ ትምህርት መርሐግብር የአንድ ዘመን የትምህርት ቀናት ከ፪፻፲ እስከ ፪፻፳ ይሆናሉ፡፡ በማታ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚኖሩት የአንድ ትምህርት ዘመን ቀናት ከ፫፻፲፭ እስከ ፫፻፳ ቀናት ወይም የአንድ ዓመት ተኩል የትምህርት ጊዜ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎች ተግባራዊ የሚሆኑበት መንገድ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል፡፡

፫/ ትምህርት በፈረቃ የሚካሄድባቸውን ሁኔታዎች አስመልክቶ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

፬/ የበዓል ቀናትን ሳይጨምር በአንድ ሳምንት አምስት የትምህርት ቀናት ይኖራሉ፡፡

፭/ በመደበኛ ትምህርት በየዕለቱ ሰባት የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ሲኖሩ እያንዳንዳቸው አርባ አምስት ደቂቃ ይኖራቸዋል፡፡ የማታው ትምህርት መርሐ ግብር በየዕለቱ አራት የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ይኖራሉ፡፡ ሀገራዊ ስታንደርዱን በጠበቀ መልኩ ክልሎች ተለማጭ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡

**33. Annual academic plan**

1/ The national academic timetable is determined by Directives issued by the Ministry. However, regions and specific areas may have different annual school schedules due to factors such as climate, parental living conditions, and natural or man-made issues.

2/ The regular school year will consist of 210 to 220 school days, while the evening session will have 315 to 320 days or one and a half school years. Detailed Directive will be issued for other alternative methods.

3/ The Ministry will issue Directive on the conditions under which education will be conducted in shifts.

4/ There are five school days in a week, excluding holidays.

5/ Regular education consists of seven periods per day, each lasting forty-five minutes. The schedule may be adjusted by regional governments in line with national standards.

https://ethiodata.et/

፮/ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና በጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊ ለሚሆኑ ተማሪዎች በሚቀረጹ መርሐ ግብሮች የሚኖረው የትምህርት ዘመን ርዝማኔ፣ የሳምንት የትምህርት ቀናት ቁጥርና የየዕለቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩-፮ የተደነገገው ቢኖርም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች የትምህርት ዓመታዊ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ ሳምንታዊ የትምህርት ቀናት፣ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ርዝመትንና የትምህርት ምጣኔን የሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ክልሎች ተቋማት ይወሰናሉ፡፡

፰/ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶችና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች የየራሳቸው የትምህርት ዓመታዊ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

## ፴፭. የራስ ሥርዓተ ትምህርት የተከለከለ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም አግባብ ባላቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጸድቆ ሥራ ላይ ባለው ሥርዓተ ትምህርት ምትክ የራሱን ሥርዓተ ትምህርት አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራቸውን የሚያካሂዱ የውጭ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶችና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች የየራሳቸው ሥርዓተ ትምህርቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ፡፡

6/ The length of the school year, number of school days per week, and number of school sessions per day will be determined by the Ministry's Directive for students with special needs and those in adult education programs.

7/ Notwithstanding the provisions of this Article, the annual school schedule for pre-primary students, weekly school days, length of school sessions, and education rate will be decided by the relevant regional education management institutions.

8/ Foreign community schools and international schools may have their own academic timetables.

## 35. Prohibition of Self-curriculum

1/ No institution of general education may issue and implement its own curriculum in place of the curriculum approved by the relevant federal and regional bodies.

2/ Notwithstanding Sub Article (1) foreign community schools and international schools operating in Ethiopia may have their own curricula.

https://ethiodata.et/

**፴፭. ሥርዓተ ትምህርትን ስለመመዘን፣ ስለመከለስና ስለማስተካከል**

፩/ የሥርዓተ ትምህርትን ተገቢነትና አፈጻጸም ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በሚወስነው መሠረት የሚካሄድ የሥርዓተ ትምህርት ምዘና፣ እንዲሁም ማስተካከያ ሥራ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

፪/ በሁሉም ዕርከን የሚገኙ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርቶች ጥናት ላይ ተመሥርቶ እንዲከለስ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ ሥርዓተ ትምህርት እንዲከለስ ሲደረግ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ ነባሩ ሥርዓተ ትምህርት ተፈጻሚ እየሆነ ይቆያል፡፡

፬/ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ለማረጋገጥ ሚኒስቴሩ በፌደራልና በክልል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትን የተመለከተ ጥናት ያካሂዳል፤ በየደረጃው ላሉ አካላትም አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፭/ ሚኒስተሩ አጠቃላይ ትምህርት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተና ዘመናዊ እንዲሁም ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃ ፣ ጥራትና አግባብነት**

**፴፮. አጠቃላይ መርሆዎች**

፩/ የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል መንግሥት ያወጣው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና እንደ አግባብነታቸው በዚህ ፖሊሲ ላይ በየጊዜው የሚደረጉት ማስተካከያዎች የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃ ጥበቃ ጥራትንና አግባብነትን በተመለከተ እንደመሪ ደንቦች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

**35. Evaluating, Revising, and Adjusting the Curriculum**

1/ To ensure the appropriateness and implementation of the curriculum, evaluation and adjustment work will be carried out as determined by the Ministry or the relevant regional body.

2/ General education curricula at all levels will be revised based on research. The details will be determined by Directive issued by the Minister.

3/ When a curriculum is revised, the existing curriculum will remain in effect until the new curriculum is fully implemented.

4/ To ensure the implementation of the provisions of this chapter, the Ministry will conduct studies on the curriculum at the federal and regional levels and provide necessary technical support.

5/ The Ministry will ensure that general education is up-to-date and effective, utilizing information communication technology.

**Part Five**

**Level, Quality, and Relevance of General Education**

**36. General Principles**

1/ The education and training policy issued by the government to improve the quality of general education, and regular adjustments to this policy, serve as a rules for maintaining the quality and relevance of general education.

https://ethiodata.et/

፪/ ሚኒስቴሩ የትምህርት ደረጃን ለማስጠበቅ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ በዚህ ረገድ በተለይ የሚከተሉትን መርሐ ግብራዊ ጉዳዮች በየወቅቱ በሚወጡ ስታንዳርዶችና መስፈርት መሠረት የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

(ሀ) የትምህርት ቤቶች ሥራ አመራር አሠራርና አደረጃጀት፣

(ለ) ትምህርት ቤቶችን በተቀመጡ ስታንዳርዶች መሠረት ማሻሻል፣

(ሐ) የመምህራን ልማትንና ብቃትን ማረጋገጥ፣

(መ) የእንግሊዝኛና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጥራት ማሻሻያ መርሐ ግብሮችን በተለይ የሚያካትት የመምህራን ልማትና ሥልጠና፣

(ሠ) ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ መጻሕፍት፣ ምዘናና የትምህርት ቁጥጥር፣

(ረ) ትምህርትና ሥልጠናን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ ውጤታማና ዘመናዊ ማድረግ፣

(ሰ) የመርሐ ግብር ቅንጅትና የአፈጻጸም ምዘና፣

፫/ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ማረጋገጫ ማስረጃ የሚሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

፬/ የትምህርት ጥራትንና አግባብነትን ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚኒስቴሩ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የምዘና ማረጋገጫውን ለመስጠት አስፈላጊውን መስፈርት በማውጣት ሥራ ላይ ያውላል፤ በብቃት እየተፈጸመ መሆኑንም ይከታተላል፡፡

2/ To fulfill the responsibility of maintaining the level of education, the Ministry will implement the following programmatic issues with relevant bodies according to standards and criteria issued periodical.

a) Function of management and organization of schools,

b) Improving schools according to set standards,

c) Ensuring teacher development and competency,

d) Teacher development and training programs, specifically including English and mother tongue quality improvement programs,

e) Curriculum and textbooks, assessment, and inspection,

f) Making education and training effective and modern through information communication technology,

g) Program coordination and performance evaluation,

3/ Certificate of the quality and relevance of general education is based on criteria specified in Sub-Article (2) of this Article.

4/ The Ministry is responsible for ensuring the relevance and continuity of the quality of education. This includes issuing necessary criteria for evaluation certification and monitoring their efficient implementation.

https://ethiodata.et/

፭/ ሚኒስቴሩ ለአጠቃላይ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብአቶችን ስታንደርድ ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፡፡

**፴፯. ሀገር አቀፍ የትምህርት ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ**

፩/ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባሮች ለማከናወን ይቻለው ዘንድ ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል አካላት እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመመካከር ሀገር አቀፍ የትምህርት ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍን ያደራጃል፡፡ በዚህም መሠረት:-

(ሀ) መሠረታዊ የሆኑ የትምህርት ጥራትና ደረጃ ማስጠበቂያ መርሆዎችን ያወጣል፣ ይህም የተማሪዎችን ክህሎት፣ እውቀት፣ እሴቶችን ባካተተ መልኩ ይቀረጻል፡፡

(ለ) በሁሉም ደረጃዎች ያሉትን የትምህርት ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ይወስናል፡፡

(ሐ) ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ ዝንባሌዎችንና ዕሴቶችን ከግምት በማስገባት የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃዎችን ይሰጣል፡፡

(መ) በትምህርት ተቋማት የሚደረጉ የግንኙነትና የመረጃ ልውውጦችን ያመቻቻል፡፡

፪/ በተጨማሪም ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል:-

(ሀ) የትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ የተቀመጡት የጥራትና የአግባብነት ደንቦች በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፡፡

(ለ) ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችልና ድግግሞሽንና ብክነትን የሚያስቀር የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

5/ The Ministry prepares the standards for educational resources needed for the teaching and learning process of general education and evaluates and controls their use.

**37. National Educational Qualification Framework**

1/ The Ministry will organize a national educational qualification certification framework in consultation with relevant federal and regional bodies and other stakeholders :

a) Establish basic principles of quality and standards of education, encompassing students' skills, knowledge, attitudes, and values.

b) Determine educational qualification criteria for all levels.

c) Provide a certificate of competency based on knowledge, skills, attitudes, and values.

d) It shall facilitate communication and information exchange conducted by educational institutions

2/ Additionally, the Ministry shall apply the following activities :

a) Ensure that quality and appropriateness of Regulations related to education are implemented.

b) Establish an education system capable of achieving desired results and avoiding duplication and wastage.

https://ethiodata.et/

፫/ አጠቃላይ ትምህርትን የሚመለከቱ ሀገር አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተል የክልል የትምህርት አስተዳደር ተቋማት ኃላፊነት ይሆናል፡፡

**፴፰. <u>የትምህርት ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት</u>**

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃና ጥራትን የሚያስጠብቅ፣ የትምህርት ክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት የሚሰጥ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እና ለዚሁ ተግባር በክልሎች የተቋቋሙ ተቋማት ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ተቆጣጣሪው፣

(ሀ) የትምህርት ደረጃና ጥራትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በትክክል በሥራ እየተተረጎሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በማንኛውም ጊዜ በአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት አባላቱን በመመደብ ሥራውን ማከናወን የሚችል ሲሆን ይህን ለማድረግ ለተመርማሪው ተቋም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መሰጠት አያስፈልገውም፡፡

(ለ) አንድ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም የሥራ መሪ፣ መምህር ወይም ማንኛውም ሠራተኛ፣ የትምህርት አሰጣጡን የጊዜ ሰሌዳና ይዘት፣ ማኅደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዲያቀርብለት መጠየቅ ይችላል፡፡ የትምህርት ተቋሙን የትምህርት አሰጣጥ ወይም አስተዳደር የሚመለከቱ መረጃዎች እንዲሰጡት መጠየቅ ይችላል፡፡

3/ Regional education management institutions are responsible for monitoring the implementation of national qualification standards for general education.

**38. <u>Educational Inspection Monitoring and Support Services</u>**

1/ The Federal Democratic Republic of Ethiopia's Education and Training Authority shall be responsible for assuring the standard and quality of general education, providing education monitoring and inspection services, and overseeing institutions established by the states for this purpose.

2/ Notwithstanding Sub Article (1) the school inspector may,

a) Assign members to general education institutions at any time to ensure correct interpretation of education level and quality issues, without needing to give advance warning.

b) Request the schedule, content of education, archives, or other documents from school directors, teachers, or employees of general education institutions.

https://ethiodata.et/

(ሐ) በምርመራ ላይ ስላለ ጉዳይ ጠቃሚ መረጃ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ የተገመተን ማንኛውንም ሰው በጽሑፍ ጠርቶ ቃለ መጠይቅ ማድረግ ይችላል፡፡

(መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መርማሪው በምርመራ ሂደት ላይ ካለው ጉዳይ ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን የትምህርት ተቋሙን አባላትና ንብረቶች ፎቶግራፎች የማንሳትና የቪዲዮ ምስሎችን የመቅረጽ ሥልጣን አለው፡፡

(ሠ) የትምህርት ቤት ሕንፃዎች፣ ሌሎች ቋሚና አላቂ ንብረቶች በአግባቡ እየተጠበቁ መሆኑን፣ የቅጥር ግቢዎችን ንጽሕናና አያያዝ፣ እንዲሁም የጽዳት አጠባበቅ በመመልከት ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ያሳውቃል፣ ለሚመለከተው አካልም ሪፖርት ያደርጋል፡፡

(ረ) የትምህርት ቤት አካባቢዎች ለመማር ምቹ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ጉድለት ካገኘም የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

፫/ የትምህርት ደረጃና ጥራት ቁጥጥርና ክትትል ሥራ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ዓይነቶችና ዕርከኖች ይካሄዳል፡፡

፬/ በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ተገቢው የትምህርት አሰጣጥ ደረጃና ጥራት ቁጥጥር በየተቋሞቻቸው እንዲካሄድ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ተቆጣጣሪዎች ሥራቸውን በሚያካሂዱ ጊዜም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፭/ የትምህርት ደረጃና ጥራት ማስጠበቂያ ቁጥጥርና ክትትል ሥራ የሚካሄደው ለተመርማሪው ተቋም አስቀድሞ በማሳወቅ ወይም ባለማሳወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

c) Sub poena and interview anyone who may provide valuable information about a case under investigation.

d) Take photographs and record video footage of members and property of educational institutions relevant to the investigation.

e) Ensure school buildings and other assets are protected, premises are clean and maintained, and report findings to the concerned body.

f) Ensure school environments are conducive to learning and suggest improvements if defects are found.

3/ Inspection and monitoring of education level and quality is conducted in all types and levels of general education institutions across the country.

4/ General education institutions have the right to request appropriate education levels and quality control for their respective institutions and must cooperate with inspectors.

5/ Inspection and monitoring of education level and quality assurance may be conducted with or without prior notification to the examining institution.

https://ethiodata.et/

፮/ ሚኒስቴሩ ተገቢው የደረጃና ጥራት ማስጠበቂያ ቁጥጥር ተካሂዶባቸው አጥጋቢ ውጤት ላስመዘገቡ የትምህርት ተቋማት ለሦስት ዓመት ዋጋ ያለው የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፯/ የሚመለከተው የሚኒስቴሩ አካል የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃ ጥራት ማስጠበቂያ ቁጥጥር ክትትል ውጤትን ዓመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡ የሪፖርቱ ቅጅም አግባብ ላላቸው የክልል የትምህርት አካላትና ተጠሪነታቸው ለፌደራሉ መንግሥት ለሆኑ የከተማ አስተዳደሮች ይላካል፡፡

፰/ መርማሪው ሲጠይቅ አንድ የትምህርት ተቋም ርዕሰ መምህር ወይም ሌላ የተቋሙ ባልደረባ የትምህርት ቤቱን መረጃዎች፣ ሪኮርዶች፣ የሂሳብ መዝገቦች፣ ማስታወሻዎች፣ የፈተና ረቂቆችንና ሌሎችም ለምርመራ ሥራው አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ቁሳቁሶችን ማቅረብ አለበት፡፡

፱/ መርማሪው ሥራውን ሲያካሂድ የሚመረመረው የትምህርት ተቋም ሥራውን ከማካሄድ መታገድ አለበት ብሎ በተጨባጭ በሚያምንበት ጊዜ የተገኘው ድክመት መወገዱ እስኪረጋገጥ ድረስ በተመርማሪው ተቋም ላይ ጊዜያዊ የዕገዳ እርምጃ እንዲጣልበት አግባብ ላለው የፌደራል ወይም የክልል የትምህርት አስተዳደር አካል የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፴፱. <u>የትምህርት ደረጃንና ጥራትን የሚመለከቱ ደንቦችን ስላለማክበር</u>**

፩/ በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በአካባቢ ደረጃ ያለው የትምህርት ደረጃና ጥራት ከተጠበቀው በታች መውረዱ ሲረጋገጥ የሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልልና የአካባቢ የትምህርት አስተዳደር ኃላፊዎች ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

6/ The Ministry will issue a certificate valid for three years to educational institutions that achieve satisfactory results and have undergone appropriate level and quality assurance control.

7/ The relevant Ministry body will submit an annual report to the Minister on the results of general education level quality assurance monitoring. A copy of the report will be sent to appropriate regional educational bodies and city governments accountable to the federal government.

8/ Upon the investigator's request, the principal or another staff member of an educational institution must provide the school's information, records, accounting records, notes, exam papers, and other materials deemed necessary for the investigation.

9/ If the investigator believes the educational institution should be suspended, they may submit a proposal to the appropriate federal or regional education management body to impose a temporary suspension until confirmed that the identified weaknesses have been addressed.

**39. <u>Non-compliance with Rules on Education Level and Quality</u>**

1/ When it is confirmed that the education level and quality at the national, regional, or local level have fallen below expectations, the relevant federal, regional, and local education management officials will be held responsible.

https://ethiodata.et/

፪/ በአንድ አጠቃላይ የትምህርት ተቋም ያለው የትምህርት ደረጃና ጥራት ከሚጠበቀው በታች የወረደ መሆኑ ሲረጋገጥ የትምህርት ተቋሙ ርዕሰ መምህርና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መምህራንና ሌሎች ለችግሩ አስተዋፅኦ ያደረጉ አካላትና ግለሰቦች ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡ የትምህርት ደረጃና ጥራት መርማሪዎችን ሥራ ለማሰናከል የሚደረጉ ተግባሮች የተከለከሉ ናቸው፡፡

፫/ በንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ላይ የተገለጸውን ተጠያቂነት በሚመለከት ትምህርት ሚኒስቴር ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፵. የክፍል ምጣኔና የማስተማር ዘዴዎች**

፩/ በአንድ የትምህርት ክፍል የሚኖረው የተማሪዎች ቁጥር መምህሩ ለእያንዳንዱ ተማሪ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ በሚያስችል መልኩ መወሰን አለበት፡፡

፪/ እንደአስፈላጊነቱ የተማሪዎቹን ቁጥር ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ወይም በግለሰብ ተማሪ ደረጃ የትምህርት አሰጣጡን ሂደት ለማሳለጥና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

፫/ የክፍሉ ተማሪዎች ቁጥር፣ የመምህርና ተማሪዎች ምጣኔን አስመልክቶ በአጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ስለሚኖረው አሠራር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ በየአካባቢዎቻቸው ያሉትን የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማትን የክፍል ምጣኔ አስመልክቶ የክልል የትምህርት ተቋማት ተገቢውን ይወስናሉ፡፡

2/ When it is confirmed that the education level and quality in a general educational institution have fallen below the set standards, the school principal, concerned teachers, and other individuals who contributed to the problem will be held responsible. Actions to disrupt the work of quality and education inspectors are prohibited.

3/ The Ministry of Education shall issue a Directive regarding the liability described in Sub-Articles (1) and (2) of this Article .

**40. Class Size and Teaching Methods**

1/ The number of students in a classroom should allow the teacher to give proper attention to each student.

2/ The number of students can be adjusted as necessary to facilitate the teaching process and benefit from information communication technology.

3/ The number of students per class, the teacher-student ratio, and the general practices of educational institutions will be determined by the Directive issued by the Ministry.

4/ Regional educational institutions will decide the class size for pre-primary education institutions in their respective areas.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ስድስት

## የተማሪዎች ምዘናና ፈተና

### ፵፩. የምዘናና የፈተና ዓላማዎች

፩/ የአጠቃላይ ትምህርት ምዘናና የፈተና ዓላማ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እየዋሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ የትምህርት ልማትን በመደገፍና የትምህርት ጥራትን በማሻሻል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

፪/ የተማሪዎችን ውጤታማነት በመለካት ረገድ ምዘናዎችና ፈተናዎች ዋና መንገድ እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች በየትምህርት ዕርከኑ ተፈላጊውን ዕውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ብስለት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ በሚያስችል መልክ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

፫/ የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ዕድገት በሚለካበት ጊዜ በአንኳር የትምህርት ዓይነቶች ያገኟቸው ውጤቶች በቀዳሚነት ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

፬/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፈተና ባይሠጥም የተማሪዎችን እድገት ለመከታተል ባሕር-መዝገብ እየተዘጋጀ በዚያው መሠረት ይመዘናሉ፡፡

፭/ እስከ አንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ (፮ኛ ክፍል) ተማሪዎችን በደረጃ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎችን ለማበረታታትና የተማሪዎችን ውጤት አገላለጽን በተመለከተ ትምህርት ሚኒስቴር እና ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

## Part Six

## Student Assessment and Examination

### 41. Objectives of Assessment and Examination

1/ The purpose of general education assessment and testing shall be to ensure the proper implementation of this Proclamation, support educational development, and improve the quality of education.

2/ Assessments and tests, as the primary means of measuring student effectiveness, shall be designed to ensure that students acquire the required knowledge, skills, and attitudinal maturity at each educational level.

3/ When evaluating the development of students' knowledge, skills, and attitudes, the results achieved in core subjects shall be taken into consideration.

4/ Although formal exams are not administered in pre-primary education, records shall be kept to monitor students' progress and they shall be evaluated accordingly.

5/ Ranking students until the completion of primary level (6th grade) is prohibited.

6/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the measures for encouraging high-achieving students and recognizing student achievement shall be determined by a Directive enacted by the Ministry of Education and the regional states.

https://ethiodata.et/

**፵፪. <u>ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውር</u>**

፩/ በሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ዕርከኖች ከክፍል ክፍል መዛወር የሚቻለው ተማሪው በተማራቸው የሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ተደምረው በአማካይ ፶ ከመቶ (፶/፻) እና በላይ በማምጣት ማለፉ ሲረጋገጥ ነው፤ አንኳር የትምህርት ዓይነቶች ዝቅተኛ የማለፊያ ውጤትን ጨምሮ ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ ወደሚቀጥለው የትምህርት ዕርከን ለመሸጋገር የሚያበቃውን ፈተና ማለፍ ያልቻለ ተማሪ ደግሞ እንዲማር የሚፈቀድለት ሲሆን፣ ይህም የትምህርት ዘመኑን የማራዘም ውጤት ይኖረዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ ተማሪዎችን መከታተልንና ማብቃትን፤ ተከታታይ ምዘናና ውጤትን መሠረት ያደረገ ማኀበራዊ የክፍል ዝውውር ተግባራዊ ይሆናል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ እና ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፵፫. <u>ፈተናዎችን የማዘጋጀትና የማስተዳደር ኃላፊነት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም ለዚሁ ዓላማ ተብሎ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ያቋቋመው የፌደራል መንግሥት አካል የ፲፪ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ብሔራዊ ፈተና የማውጣትና የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የ፲፪ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የሚሰጥባቸውን የትምህርት ዓይነቶች ይወስናል፡፡

፫/ አንድ ተማሪ አጠቃላይ ትምህርትን የሚያጠናቅቀው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚሠጠውን ፈተና ሲወስድ ነው፡፡

**42. <u>Promotion From One Grade Level to the Other</u>**

1/ In all levels of general education student may be promoted to the next class when they achieve an average score of 50% or more in all subjects studied. A lower passing grade may be applied to core subjects, as determined by the Directive issued by the Ministry.

2/ A student who fails to pass the exam required for the next level of education shall be allowed to continue studying, which may extend the duration of their education.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article Social class transfer based on monitoring and empowering students up to the fourth grade shall be implemented, the detaile Directive issued by the Ministry of and the regional states.

**43. <u>Responsibility for Developing and Administering Examinations</u>**

1/ The Minister, or a representative or body duly established by the Council of Ministers, shall be responsible for developing and administering the National Examination for the completion of Grade 12.

2/ The Ministry shall determine the type of subjects given for grade 12 final examinations.

3/ A student complete general education upon taking the exam as specified in Sub-Article 1 of this article.

https://ethiodata.et/

፬/ የስድስተኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና በክልል ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን ዝግጅቱም ሆነ አስተዳደሩ በክልል ትምህርት ቢሮዎች ስታንደርዱን ጠብቆ ይከናወናል፡፡ ለዚህም ክልሎች በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን ስታንደርድ መሠረት በማድረግ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በማውጣት ይተገብራሉ፡፡

፭/ የስምንተኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና አዘገጃጀት ስታንደርድ በትምህርት ሚኒስቴር ይዘጋጃል፤ ፈተናውን የማዘጋጀትና የማስተዳደር ሥራ በክልል ትምህርት ቢሮዎች ይከናወናል፡፡

፮/ በሌሎች የትምህርት ክፍሎች ፈተናዎችን የማውጣትና የማስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት የእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ይሆናል፡፡

## ፵፬. ለፈተና የመቀመጥ መብት

፩/ አንድ ተማሪ በክልል እንዲሁም ሀገር አቀፍ ፈተና በሚሰጥበት ጊዜ ተፈታኝ መሆን የሚቻለው ፈተናው በሚሰጥበት የትምህርት ደረጃ እየተማረ ባለበት ዓመት ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ተማሪው ክልላዊ ፈተና በቀጣዩ የትምህርት ዓመት ብቻ በተለየ ሁኔታ ደግሞ በመማር ለሁለተኛ ጊዜ መፈተን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተሠጠው ዕድል ተጠቅሞ ፈተናውን ማለፍ ያልቻለ ተማሪ ከዚያ በኋላ በግሉ መፈተን ይችላል፡፡

4/ The Grade 6 final exam shall be administered at the regional level, with preparation and administration carried out by regional education offices in accordance with established standards. Detailed implementation Directives shall be issued by the regional governments based on ministry standards.

5/ The standards for preparing the Grade 8 final exam shall be prepared by the Ministry of Education, with the preparation and administration of the examination conducted by regional education offices.

6/ The responsibility for developing and administering exams in other grade levels shall rest with each educational institution.

## 44. Right to Sit for Examination

1/ Students may sit for a regional or national exam during the academic year in which they are studying at the level of education for which the exam is given.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) , students may retake the regional exam once in the next academic year under special circumstances.

3/ A student who fails to pass the exam after using the opportunity given in Sub-Article (2) may take the exam privately.

https://ethiodata.et/

፬/ ከላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ፈተናውን ወስዶ ያለፈ ተማሪ ወደሚቀጥለው ክፍል ገብቶ ለመማር ይችላል።

**፵፭. የተፋጠነ ዝውውር እና ትምህርት**

፩/ ፈጣን የአእምሮ እድገትና የመማር ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ከክፍል ክፍል ዝውውር የትምህርት ካላንደሩን ሳይጠብቅ በሴሚስተር ሊፈጸም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ተማሪው ሀገር አቀፍና የክልል ፈተናዎችን ተፈትኖ ሳያልፍ ወደሚቀጥለው የትምህርት ዕርከን መሻገር አይችልም፡፡

፫/ በተፈጥሮ አደጋና በሰው ሰራሽ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ እና ትምህርት በመጀመሪያ እድሜያቸው ትምህርት ያልጀመሩ ዜጎችን ከመደበኛው ትምህርት በተለየ መልኩ በአጭር ጊዜ ከእድሜ እኩያቸው ጋር እንዲስተካከሉ ለማድረግ የሚያስችል የተፋጠነ የትምህርት መርሃ ግብር ተግባራዊ ይደረጋል፤ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፵፮. ማስረጃ የማግኘት መብት**

፩/ ተማሪዎች የተለያዩ የትምህርት ዕርከኖችንና የክፍል ደረጃዎችን ሲያጠናቅቁ ከሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ወይም ከሚመለከተው የክልል ወይም የፌደራል መንግሥት አካል ተገቢውን የምስክር ወረቀት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፪/ የምስክር ወረቀቶቹ ተማሪው በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ያገኘውን ውጤትና ከአንድ ክፍል ወደሚቀጥለው የሚደረገውን የዝውውር መስፈርት የሚገልጹ ሊሆኑ ይገባል፡፡

4/ In accordance with the above Sub-Article (3), a student who has taken and passed the examination shall be eligible to advance to the next grade.

**45. Accelerated Transfer and Education**

1/ Students with high intellectual development and learning ability may be promoted from one grade level to another within a semester without waiting for the academic calendar.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1), students may not advance to the next level of education without passing the national and regional exams.

3/ An accelerated education program shall be implemented to enable individuals who have dropped out of school due to natural disasters or human-made causes, as well as those who did not enroll at the appropriate age, to catch up with their age peers within a shorter period than the standard education timeline. The criteria and implementation procedures shall be determined by Directive issued by the Ministry.

**46. Right to Evidence**

1/ Students are entitled to receive appropriate certificates from the schools they attend or from the relevant regional or federal government body upon completing various levels of education.

2/ The certificates shall have the student's grades in each subject and the criteria for transferring from one grade to the next.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሰባት

## ስለ አጠቃላይ ትምህርት መምህራን

### ፵፯. መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ ሁሉም የትምህርት መርሐ ግብሮች ሊቀረጹ የሚገባው መምህራን ለሰው ልጅ ደህንነት እና ለሀገር ዕድገት በሁሉም ዘርፎች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከግምት በማስገባት ተገቢውን እውቅና በመስጠት መሆን አለበት፡፡

፪/ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት መምህራን ተፈላጊው የሙያ ፍቅር፣ ችሎታ፣ ትጋትና ብቃት ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፫/ መምህርነት የተከበረ ሙያ መሆኑን በመገንዘብ የመንግሥት አካላት እና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ክብርና ጥቅም እንዲሰጠው ማድረግ ይገባል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፵፰. የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና

፩/ የመምህራን ምልመላና ሥልጠና ሥራ መምህራን በግልና በጋራ ተፈላጊው የሙያ ብቃት ኖሯቸው ትምህርት እንዲስፋፋና ዕውቀትም እንዲበለጽግ የሚያደረግ ይሆናል፡፡

፪/ የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና በሠርተፍኬት፣ በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፤ በማስተርስ ዲግሪ እና በሌሎች በሚኒስቴሩ በሚወሰኑ ደረጃዎችና መርሐ ግብሮች ይከናወናል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ መምህራን የሚመለመሉበትንና የሚሰለጥኑበትን ሁኔታዎች በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

## Part Seven

## General Education Teachers

### 47. Basic Principles

1/ All educational programs shall be designed with due recognition of the contributions of teachers to human welfare and national development in all sectors.

2/ Relevant government bodies shall ensure that teachers possess the required professional passion, skills, dedication, and competence.

3/ Recognizing that teaching is a respected profession, public bodies and all members of society shall accord teachers appropriate respect and recognition. The specific details shall be determined by Directives issued by the Minister.

### 48. Teacher education and training

1/ The recruitment and training of teachers shall ensure that teachers individually and collectively possess the required professional qualifications to enhance education and knowledge dissemination.

2/ Teacher education and training shall be conducted at various levels, including certificate, diploma, first degree, and Master's degree, as determined by the Ministry.

3/ The Ministry shall issue Directives regarding the conditions under which teachers are recruited and trained.

https://ethiodata.et/

፬/ ወደ መምህርነት ሙያ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው አመልካቾች ውጤታማ የትምህርትና የሥልጠና አገልግሎት እንዲያገኙ የፌደራልና የክልል መንግሥታት ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ፤ በቂ በጀትም ይመድባሉ፡፡

፭/ የመምህራን ትምህርት፣ ሥልጠናና አደረጃጀት በቅድመ ሥራና በሥራ ላይ ሥልጠና መልክ በሚቀረጹ መርሐ ግብሮች ይከናወናል፡፡

፮/ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ለመምህርነት ስልጠና በሚወዳደሩበት ጊዜ ለምልመላ የሚያስፈልጉትን አጥጋቢ መስፈርት አሟልተው በውድድር ወቅት ከወንዶች ጋር እኩል ነጥብ በሚያገኙበት ጊዜ ቅድሚያ ይሠጣቸዋል፡፡

፯/ አንድ መምህር በሥራ ላይ እያለ በመንግሥት ወጪ ደረጃውን የሚያሻሽል ሥልጠና ከወሰደ ለእያንዳንዱ የሥልጠና ዓመት አንድ ዓመት በሙያው ማገልገል አለበት፡፡

፰/ የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚመሠረቱበትና ሥራቸውንም የሚያካሂዱበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፱/ በመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያስተምሩ ባለሙያዎች በሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ ባለሙያዎች ሊያሟሉ የሚገባውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡ በተለይም የማስተማር ዘዴን የሚመለከቱ የትምህርት ዓይነቶችን የሚያስተምሩ ባለሙያዎች ከአካዳሚያዊ ብቃት በተጨማሪ በሙያው ልምድ ያካበቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

4/ Federal and regional governments shall ensure that applicants interested in becoming teachers receive effective education and training services and allocate an adequate budget for this purpose.

5/ Teacher training and organization shall be conducted through programs designed for both pre-service and in-service training.

6/ Women and persons with disabilities who meet the required qualifications for teacher training shall be given priority in recruitment when competing with other candidates and obtaining equal scores.

7/ Teachers who receive training at the government's expense while on the job must serve one year in the profession for every year of training.

8/ The conditions for establishing and operating teacher education and training institutions shall be determined by Regulations issued by the Council of Ministers.

9/ Professionals teaching in teacher education and training institutions must meet the same requirements as those teaching in other higher education institutions. Specifically, teachers of pedagogy should have professional experience in addition to academic qualifications.

https://ethiodata.et/

፲/ በሥልጠናው ተሳታፊ የሚሆኑና በመንግሥት የትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ወይም የትምህርት ሥራ ተቆጣጣሪዎች ለሥልጠናው ምንም ዓይነት ክፍያ እንዲፈጽሙ አይጠየቁም፤በግል ትምህርት ቤት ላሉት ባሙያዎች የሚደረገውን የሥልጠና ወጪ ቀጣሪው አካል ይሸፍናል፡፡ የክፍያውን መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ አስመልክቶ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፵፱. <u>የርእሰ መምህራን፣ የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች አቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች</u>**

፩/ ለመምህራን አቅም ግንባታ መርሐ ግብር የሚቀረጹ ኮርሶች የሠልጣኞቹን ዕውቀትና ችሎታ በማሻሻል፣ የሥራ መስኮቻቸውን ለማስፋት ወይም ወደሌላ ለመለወጥ፣ ወይም በሚያስተምሯቸው የትምህርት ዘርፎች ዙሪያ ከተከሰቱ አዳዲስ አስተሳሰቦችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በማስተዋወቅ ላይ የሚያተኩሩ ይሆናሉ፡፡

፪/ የትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራን፣ ሌሎች መምህራንና የትምህርት ሥራ ተቆጣጣሪዎች (ሱፐርቫይዘሮች) የሙያ ደረጃቸው ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ሚኒስቴሩ ተከታታይ የሥልጠናና የሙያ ማበልጸጊያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

፫/ እያንዳንዱ ርዕስ መምህር፣ መምህርና የትምህርት ሥራ ተቆጣጣሪ በዚህ ዓይነቱ ሥልጠና ተሳታፊ የመሆን ግዴታ አለበት፡፡

፬/ የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት፣ አስተዳደር፣ ክብር እና ጥቅማ ጥቅምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወጣል፡፡

10/ Principals, teachers, and educational inspectors who undergo training and serve in government educational institutions shall not be required to pay for such training. The cost of training for professionals in private schools shall be covered by their respective employers. The Ministry shall issue Directives regarding the amount of fees and the conditions for their allocation.

**49. <u>Capacity Building Programs for Principals, Teachers, and Education Professionals</u>**

1/ Courses designed for teacher capacity building shall focus on improving the knowledge and skills of trainees, expanding or changing their fields of work, or introducing them to new ideas and teaching methods.

2/ The Ministry shall establish a continuous training and professional development system for school principals, teachers, and educational work supervisors to ensure their professional level aligns with current conditions.

3/ Every subject teacher and education supervisor is obliged to participate in such training.

4/ The Council of Ministers shall issue Regulations regarding the development, administration, status, and benefits of teachers and educational leaders.

https://ethiodata.et/

፭/ በአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፲ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚያስተምረው አጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የሰለጠነና ተጨማሪ የማስተማር ሥነ ዘዴ ወስዶ በመምህርነት ሙያ ላይ የተሰማሩትን በሥራቸው እንዲቀጥሉ የሚያስችል ሥልጠና የሚሰጥ ይሆናል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፭ የተደነገጉት መንግሥታዊ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፶. <u>በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ስለሚደረግ ምደባ</u>**

፩/ በመንግሥት የትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ መምህራን ምደባ የሚካሄደው በክልል የትምህርት ቢሮዎችና አግባብ ባለው የዞን ወይም የወረዳ የትምህርት አስተዳደር አካል ነው፡፡

፪/ አንድ አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥ ተቋም ለሚያስተምራቸው የትምህርት ዓይነቶች በቂ ቁጥር ያላቸው መምህራን የመመደብ ወይም እንዲመደቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ ወሲባዊ ጥቃትን የሚመለከቱ ወንጀሎች መፈጸሙ ተረጋግጦ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠበት ሰው በማንኛውም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም ውስጥ መምህር ሆኖ ሊቀጠር አይችልም፡፡ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ በመምህርነት ሥራ ተሰማርቶ የወሲባዊ ጥቃት ወንጀል መፈጸሙ የተረጋገጠበትን ሰውም ይጨምራል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለተከው ድንጋጌ በዚህ ወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ የተሰየመን ሰው አይጨምርም፡፡

5/ In accordance with Sub-Article (10) of Article 2, the general education sector shall ensure that educators receive the necessary training and additional teaching methodology to maintain and enhance their qualifications for continued service in the teaching profession.

6/The provisions of Sub-Article (1) to (5) of this Article shall also apply to non-governmental educational institutions.

**50. <u>Placement in Government Schools</u>**

1/ The assignment of teachers in government educational institutions shall be managed by regional education offices and the appropriate zonal or district education management bodies.

2/ Each general education institution shall be responsible for ensuring that a sufficient number of teachers are assigned to the subjects it teaches.

3/ Individuals found guilty of sexual violence in a court of law shall not be employed as teachers in any general education institution. This provision also applies to current teachers who have committed sexual violence.

4/ The provisions in Sub-Article (3) shall not apply to individuals exonerated of such crimes.

https://ethiodata.et/

## ፶፩. <u>የሥራ ዕድገትና ከሥራ መልቀቅ</u>

፩/ ግልጽና በተጨባጭ ሊለካ በሚችል መስፈርት ላይ በመመሥረት ሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን ከአንድ የማስተማር ዕርከን ወደ ሌላው ወይም ከአንድ የሙያው ደረጃ ወደቀጣዩ የመሸጋገር መብት አላቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው መስፈርት የመምህሩን የግል የሥራ ብቃትና የሚያከናውነውን ሥራ ክብደት ከግምት የሚያስገባ መሆን አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተው ቢኖርም የትምህርት ተቋሙ ሲፈልገውና መምህሩም ሲስማማ ጥቅማጥቅሙ ተጠብቆለት ባለበት ዕርከን ላይ መቆየት ይችላል፡፡

፬/ በሚኒስቴሩ የሚወጣው የመምህራን ሙያ ማእቀፍ በሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማትና በሁሉም የሙያው ዕርከኖች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭/ በየእርከኑ ባሉት የመምህርነት ሙያዎች መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርት፣ መምህራን ከአንዱ የማስተማር ዕርከን ወደሌላው ወይም ከአንዱ የማስተማር ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ እድገት ሊያገኙ ስለሚችሉበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

፮/ ሥራ መልቀቅን በተመለከተ የአገልግሎት ግዴታ የሌለበት መሆኑ ተጣርቶ አግባብ ባለው ሕግ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 51. <u>Promotion and Dismissal</u>

1/ Based on a clear, empirically measurable criterion, all general education teachers have the right to move from one teaching step to another or from one stage of the profession to the next.

2/ The requirement mentioned in Sub-Article (1) of this Article must take into account the teacher's personal work performance and the severity of the work that they perform.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the educational institution can remain on a terrace where the benefit is reserved for it when it needs it and the teacher agrees.

4/ The teacher professional framework issued by the Ministry shall apply to all general education institutions and all levels of the teaching profession.

5/ The Ministry shall issue Directives regarding the requirements for each teaching level and the conditions under which teachers may be promoted from one level to another.

6/ In the case of resignation, it shall be determined and enforced in accordance with the applicable law, after clarifying that the employee has no remaining service obligations.

https://ethiodata.et/

**፶፪.የመምህራን የሥራ እና ሙያ ፈቃድ**

፩/ ሚኒስቴሩ የመምህራን የስራ ፈቃድ አሠጣጥን፣ የሥራ አፈጻጸም ክትትልን፣ ዕድገትን እንዲሁም የሙያ ፈቃድ ዕድሳትን የሚመለከት ስታንዳርድ በመመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ተገቢው የማስተማር ሥራ ፈቃድ ሳይኖረው በአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመምህርነት መቀጠር አይችልም፡፡

፫/ ከቅድመ ሥራ ላይ ስልጠና በኋላ በመምህርነት የሚመደብ ሰው በቅድሚያ የሁለት ዓመት የትውውቅ ሥልጠና የመከታተልና ለዚህም የሚሰጠውን የመመዘኛ ፈተና የማለፍ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ግዴታ ከተወጣ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው የሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፬/ አንድ መምህር ከደረጃ ዕድገት ቆይታ ጋር በተሳሰረ መልኩ የሙያ ፈቃዱን ማሳደስ ያለበት ሲሆን የእድሳቱ አገልግሎት ከማንኛውም ክፍያ ነፃ ይሆናል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸውን መምህራን የሙያና የሥራ ፈቃድ እና ዕድሳት በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፶፫. የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የሥራ ዋስትና**

፩/ ማንኛውም መምህር በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ግዴታ አለመወጣቱ አግባብ ባለው አካል ካልተረጋገጠ በስተቀር ከራሱ ፈቃድ ውጭ ከሥራ አይሰናበትም፡፡

**52. Teachers' Work and Professional Licensing**

1/ The Ministry issues work permits, monitors performance, establishes promotion and license renewal standards, and facilitates implementation with relevant regional bodies.

2/ No person can be employed as a teacher without the appropriate teaching license.

3/ A teacher assigned after preliminary on-the-job training must attend a two-year familiarization training and pass a qualification test to receive the work permit according to Sub Article (1) of this specific provision.

4/ Teachers must renew their professional license every two years during the promotion period, free of charge; The Ministry shall issue Directives on detailed matters.

5/ The Ministry will issue directives for the professional and work permit renewal for foreign teachers.

**53. Job Security of General Education Teachers**

1/ No teacher shall be dismissed without consent unless it is confirmed by the appropriate body that they have not fulfilled their responsibilities and duties.

https://ethiodata.et/

፪/ መምህራን በሚያስተምሩበት ተቋም ወይም በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የመዋቅር ለውጥ ቢደረግም እንኳ ዋስትናቸው ተከብሮ ይቆያል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም መምህራን የትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በሚኖረው ለውጥ ራሳቸውን እንዲያበቁ ይደረጋል፡፡

፬/ መምህራን እና የትምህርት አመራሮች በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ወይም ሕይወት ማለፍ ምክንያት ለተጎጂው ወይም ለተተኪዎች በመንግሥት ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ በፌደራል አሠሪና ሠራተኛ ሕጉ በተደነገገው መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ፶፬. <u>የሙያ ነፃነት</u>

፩/ መምህራን ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚወጡበት ጊዜ የተሟላ የአካዳሚና የሙያ ነጻነት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ መብት በተለይ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ይሆናል:-

(ሀ) በጸደቁ መርሐ ግብሮችና ሥርዓት ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው ለተማሪዎች ይበጃል በሚሉት የማስተማር ዘዴና የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች ሥራቸውን የማካሄድ፣

(ለ) በተከታታይ ምዘናና ወቅትን ጠብቀው በሚሰጡ ፈተናዎች የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ብቃት የመመዘን፣

2/ Teachers' job security will be respected even with structural changes in the institution or education system.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub Article (2) of this Article, teachers will be required to engage in ongoing professional development to adapt to changes in the education system.

4/ Teachers and educational leaders who work in government education institutions and whose employment is affected by injury or death shall be compensated according to the Proclamations for federal government employees. Similarly, non-government educational institutions shall comply with the provisions of the Federal labor law.

## 54. <u>Occupational Freedom</u>

1/ Teachers will have complete academic and professional freedom in performing their duties and responsibilities, including:

a) Using the best teaching methods and teaching aids within approved programs and systems,

b) Assessing students' academic performance through continuous and periodic assessments,

https://ethiodata.et/

፪/ የትምህርት ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓቱ መምህራን ኃላፊነቶቻቸውን በሚገባ እንዲወጡ ለማበረታታት በሚያስችል መልክ መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው የቁጥጥር ሥርዓቱ ይህን የመምህራንን ነጻነትና የሙያ ተነሳሽነት በሚሸረሽር አኳኋን መካሄድ አይኖርበትም፡፡

፫/ የመማር ማስተማር ሂደቱን ጥራትና ተገቢነት አስመልክቶ መምህራን አስፈላጊውን ሀሳብ የመስጠት መብት አላቸው፡፡

**፶፭. <u>የመምህራን የሥነ ምግባር ደንብ</u>**

፩/ መምህራን ተቀባይነት ባላቸው መርሆዎች መሠረት የሚያበረክቱትን የላቀ አገልግሎትና የሙያውንም ክብር ከፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ሚኒስቴሩ መምህራን በማኅበራቸው አማካይነት የራሳቸውን የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ እንዲያወጡ ይደግፋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ዝርዝር አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

**፶፮. <u>የሙያ ኃላፊነትን ስላለመወጣት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ወይም በሙያው የሥነ ምግባር ደንቦች የተመለከቱትን ተግባርና ኃላፊነቶች በማይወጡ መምህራን ላይ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አስመልክቶ የዲሲፕሊን መመሪያ ያወጣል፡፡

2/ The educational controlling and monitoring system should be developed to encourage teachers in effectively fulfilling their responsibilities. On the contrary, the regulatory system should not be conducted in a manner that erodes the professional freedom and motivation of teachers.

3/ Teachers have the right to make suggestions regarding the quality and appropriateness of the teaching and learning process.

**55. <u>Code of Conduct for Teachers</u>**

1/ To uphold the excellence of service and the dignity of the teaching profession in accordance with established principles, the Ministry shall encourage teachers, through their professional associations, to develop their own code of professional conduct.

2/ The Ministry shall also be responsible for overseeing its implementation.

**56. <u>Failure to Fulfill Professional Responsibility</u>**

1/ Appropriate action will be taken against teachers who fail to perform their duties and responsibilities as stipulated in this Proclamation, related Directive and Regulations, or the professional code of conduct.

2/ The Ministry will issue a disciplinary Directive in this regard.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጸው ድንጋጌ ቢኖርም መምህራን የሙያ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት በሌሎች ላይ ለሚፈጽሙት ጥፋት አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ስምንት

## የትምህርት አስተዳደርና አመራር

### ፶፯. ያልተማከለ አስተዳደር

፩/ የትምህርት አስተዳደርና አመራር ሁሉንም የትምህርት ባለድርሻዎች ሊያሳትፍ በሚችልበት አኳኋን ባልተማከለ የሥራ የሥልጣን ተዋረድና አስተዳደር ይካሄዳል፡፡

፪/ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እንዲሁም በእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ደረጃ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብና መመሪያዎች መሠረት በትምህርት አስተዳደርና አመራር ጉዳዮች ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተገለጹት መንግሥታዊ ባለድርሻ አካላት በተጨማሪ ወላጆችና የወላጆች ማኅበራት፣ ተማሪዎች፣ የመምህራን ማህበር፣ የሚመለከታቸው የሲቪል ማኅበረሰብ አባላት፣ አግባብ ያላቸው የጥናትና ምርምር ተቋማትና ታዋቂ ግለሰቦች፣ የቀድሞ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግንባታና ልማትን አስመልክቶ ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡

፬/ ባለድርሻ አካላቱ በተለይም በወረዳ፣ በቀበሌና በትምህርት ቤት ደረጃ በሚቋቋም የትምህርትና ሥልጠና ቦርድ ውስጥ ውክልና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

3/ No Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) of this Article teachers will be liable under relevant laws for offenses committed by not fulfilling their professional responsibilities.

## Part Eight

## Education Administration and Leadership

### 57. Decentralization

1/Education management and leadership will involve all stakeholders in a decentralized hierarchy of work and authority.

2/ Federal, Regional, zonal, district, and educational institution stakeholders will participate in education management and leadership per this Proclamation and related Regulations.

3/ In addition to the governmental stakeholders defined in Sub-Article (2) of this Article, parents and parent associations, students, teacher associations, relevant civil society members, appropriate research institutions, distinguished individuals, and alumni shall be involved in accordance with the Ministry's Directives on school construction and development.

4/These stakeholders shall have designated representation in the Board of Education and Training, which shall be established at the district, kebele, and school levels.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ዘጠኝ

## የትምህርት ድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶች

**፶፰. የትምህርት ተቋማት ግንባታና መገኛ ቦታ**

፩/ የትምህርት ተቋማት ግንባታና የመገኛ ቦታዎች የጥራት ደረጃ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ስታንዳርድ ይወስናል፡፡

፪/ ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን እንዲሁም ባለባቸው የአካል ጉዳት ሳቢያ ድጋፍ የሚስፈልጋቸውን ተማሪዎችን ጨምሮ ለሁሉም ለተማሪዎች የተመቹና አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሁኔታዎችና አካባቢዎች የጸዱ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ ማንኛውም የትምህርት ተቋም ከገበያ ቦታ፣ ከመጠጥ ቤቶች፣ ከዋና መንገዶች እንዲሁም በድምፅና በአየር ብክለት ከተጠቁ ቦታዎች እና ከሌሎች በተማሪዎች ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ስፍራዎች እንዲሁም ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ስራዎች ከሚከናወኑበት ስፍራ ርቆ መቋቋም አለበት፡፡

፬/ ቀደም ብለው የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች እና በንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይከናወኑ የሚከለክል ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወጣል፡፡

**፶፱. የትምህርት ቴክኖሎጂ ደረጃ አሰጣጥ**

፩/ የማስተማርያ መጻሕፍት፣ ሌሎች የትምህርት ድጋፍ ሰጪ ዕቃዎችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ከመደረጉ በፊት ሊያሟሉ የሚገባውን የጥራት ደረጃና የመማሪያ መስፈርት አስመልክቶ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

## Part Nine

## Educational Support Services

**58. Construction and Location of Educational Institutions**

1/ The quality and location standards for educational institutions are determined by the Ministry.

2/ Schools should be comfortable for all students, including those with special needs and physical disabilities, and free from dangerous conditions and environments.

3/ Educational institutions should be located away from markets, pubs, main roads, noisy areas, polluted areas, and other places that negatively impact students' development. Commercial activities contrary to morality should not be conducted nearby.

4/ A Regulation shall be issued by the Council of Ministers prohibiting businesses, that fall under Sub-Article (2) and (3) and are contrary to public welfare, from operating near educational institutions.

**59. Educational Technology Standardization**

1/ The Ministry will issue Directives on the quality and learning standards for textbooks, educational support items, and technological products before importation.

https://ethiodata.et/

፪/ የትምህርት ቴክኖሎጂ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በፍትሐዊነት እየተሰራጨ መሆኑ በሚኒስቴሩ ይረጋገጣል፡፡

፫/ አግባብ ያላቸው የንግድና የቅጅ መብቶችን የሚመለከቱ ሕጎችና ሀገሪቱ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ሚኒስቴሩ የግሉ ዘርፍ በትምህርት መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂ ማምረትና ማዳበር ሥራ እንዲሳተፍ ያበረታታል፡፡

፬/ የትምህርት መልቲ ሚዲያ ፕሮግራሞች ማለትም በሬዲዮ ፣ በቴሌቭዥን ፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ፣ በኢንተርኔትና በተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚካሄዱ መርሐ ግብሮች ዝግጅትና ስርጭት አግባብ ባላቸው ሕጎችና ሀገሪቱ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የገባቻቸውን ግዴታዎች በጠበቀ ሁኔታ ይሠጣል፡፡

፷. **ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሙከራዎችና የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት**

፩/ ማንኛውም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን ደረጃ የጠበቀ ወይም የጠበቁ ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሙከራዎችና የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

፪/ ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሙከራዎችና የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፍና ሥራ ላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት በሚያግዝ መልክ መደራጀት አለባቸው፡፡

፫/ መንግሥት ቤተ ሙከራዎችና የትምህርት ማበልጸጊያ መጻሕፍትና መሣሪያዎች ከውጭ ሀገር ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ለሁሉም ዓይነት የትምህርት ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

2/ The Ministry will ensure fair distribution of educational technology across the country.

3/ The Ministry encourage private sector participation in producing and developing educational equipment and technology, subject to relevant commercial and copyright laws and international agreements.

4/ The preparation and distribution of educational multimedia programs, i.e. radio, television, mobile phone, Internet and similar technological products, shall be carried out in compliance with the relevant laws and the obligations of the country under international agreements signed.

60. **Libraries, Laboratories, and Pedagogical Centers**

1/ General education institutions must have libraries, laboratories, and educational enhancement centers meeting Ministry standards

2/ libraries, laboratories, and educational enhancement facilities should be Established to support the teaching and learning process of the existing curriculum.

3/ The government will support educational institutions to import labs, supplementary books, and equipment tax-free.

https://ethiodata.et/

**፷፩. የተማሪዎች ምክር አገልግሎት**

፩/ በየትኛውም ዕርከን ላይ ያሉ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎቻቸው ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ በዘርፉ በሠለጠኑ ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ የምክር አገልግሎቱ በተለይ የትምህርት አቀባበል ችግሮችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ የዲሲፕሊንና የሥነ ልቦና ጉዳዮችን፣ አካል ጉዳተኝነትን፣ ሥነ ጾታን፣ ኤች አይቪ ኤድስን በሚመለከቱ ችግሮች ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፡፡

፫/ ማንኛውም ተማሪ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከቱ አገልግሎቶችን ትምህርት ቤቱ የምክር አገልግሎት እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት ያለው ሲሆን በተለይም ለኤች አይ ቪ ኤድስ የተጋለጡ ወይም ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቻቸው ወይም ለዚሁ ተግባር በተቋቋሙ ሌሎች አካላት ተገቢውን የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**፷፪. የተማሪዎች ንጽሕናና ጤንነት አጠባበቅ**

፩/ ማንኛውም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም በቅጥር ግቢው ተገቢው የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ እንዲሁም ማናቸውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታን ጨምሮ መሠረታዊ የሕክምና አገልግሎት መስጫ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ትምህርት ቤቱ መሠረታዊ የህክምና አገልግሎት ከሌለው አገልግሎቱ በጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጣቢያ ይሰጣል፡፡

**61. Student Counseling Service**

1/ General education institutions are responsible for providing counseling services from trained professionals starting from the first grade.

2/ Counseling will focus on educational reception, harmful customs, disciplinary and psychological issues, disability, sexuality, and HIV-AIDS.

3/ Students have the right to request counseling services stated on Sub Article (2) of this Article , it must be be provided for students exposed to or living with HIV in the school yard or by other institutions established to provide councling services .

**62. Hygiene and Health Care of Students**

1/ Every institution of general education shall have basic medical services, including first aid, on its premises. Any middle level education institution shall have adequate first aid.

2/ If the school lacks basic medical services as per Sub Article (1) of this Article, these services will be provided by the health extension service station.

https://ethiodata.et/

፫/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃና በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ሕፃናት አግባብ ባላቸው የጤና አካላት የተወሰኑትን መሠረታዊ ክትባቶች መውሰዳቸውን ማረጋገጥ የሚማሩባቸው ተቋማት ኃላፊነት ነው፡፡

፬/ አንድ አጠቃላይ የትምህርት ተቋም በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ በዓመት አንድ ጊዜ የጤና ምርመራ እንዲያካሂዱ ያደርጋል፡፡

፭/ ሁሉም አጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ንጹሕና በቂ የመጠጥ ውሃ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቅጥር ግቢና የተለያዩና የተራራቁ የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች፣ የመምህራን መጸዳጃ ክፍሎች እንዲሁም ከ፭ኛ ክፍል ጀምሮ ለሴት ተማሪዎች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ የመቀየሪያ ክፍል መኖራቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡

፮/ አንድ ተማሪ ሌሎች ተማሪዎችን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሊድን በሚችል ተላላፊ ሕመም እየተጠቃ መሆኑ ሲታወቅ ከሕመሙ ሙሉ በሙሉ መፈወሱ በሕክምና እስኪረጋገጥ ድረስ የሕክምና ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ድኖ ከተመለሰም በኋላም የቀረበትን ትምህርት ለማካካስ ትምህርት ቤቱ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፮ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች አፈፃፀሙን በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ At the pre-primary level, it is the responsibility of educational institutions to ensure that children studying in primary and middle level schools receive certain basic vaccinations from relevant health authorities.

4/ General educational institutions shall, as far as possible, have their students undergo a health check-up once a year.

5/ All general education institutions shall ensure the availability of clean and adequate drinking water, well-maintained classrooms, and appropriate school premises. They must also provide separate restrooms for male and female students, as well as restrooms for teachers. Additionally, starting from the 5th grade, schools shall supply necessary hygiene materials for female students..

6/ When a student is found to be suffering from a curable infectious disease that poses a danger to other students, they will be given medical leave until their complete recovery from the disease is medically confirmed. Even after recovery, the school will make every effort to help them make up for missed lessons.

7/ The Minister shall issue Direcctives for the implementation of the provisions set forth in Sub-Article (1) to (6) of this Article.

https://ethiodata.et/

**ክፍል አሥር**

**ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርት**

**፷፫. የልዩ ፍላጎት ትምህርት አሰጣጥ**

፩/ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አጠቃላይ ትምህርትን በተመለከተ ከሌሎች ተማሪዎች ዕኩል በአካትቶ ትምህርት ይማራሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በአካትቶ ትምህርት መማር ለማይችሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የጤናና የአካል ጉዳት ላለባቸው ዜጎች የሚሰጥ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል:-

(ሀ) የመማር ወይም የባህርይ ችግር ያለባቸው፣ አካላዊ ጉዳት ያለባቸው፤ መስማት የተሳናቸው፣ ዐይነ ስውራን፡ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው፤ የተግባቦት ቋንቋ እጥረት ያለባቸው፤ በከፍተኛ ሕመም የሚሰቃዩትንና ኦቲስቲክ የሆኑ ሕፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች፣

(ለ) ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሕፃናት፣

፬/ ሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያለባቸው ተደራራቢ ተጋላጭነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡

**Part Ten**

**Education of Students with Special Needs**

**63. Delivery of Special Needs Education**

1/ Students with special needs receive inclusive education on par with other students in general education.

2/ Subject to the provisions of Sub Article (1) of this Article, the Ministry will issue Directives regarding the provision of education to students with disabilities who cannot attend inclusive education due to force majeure.

3/ Special needs education is provided to citizens with health and physical disabilities and includes the following:

a) Those with learning or behavioral problems, physical disabilities; deaf, blind, mentally retarded; those who lack communicative language; children, youth, and adults with severe illness and autism,

b) Children with multiple disabilities,

4/ Female students with disabilities shall receive special support, taking into account the multiple challenges they face.

https://ethiodata.et/

## ፷፬. ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ስላላቸው ተማሪዎች

፩/ ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ኖሯቸው ይህን ዕምቅ ችሎታ የበለጠ ያዳብሩ ዘንድ ትኩረትና ክትትል ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መንግሥት የተለየ ትኩረት ያደርጋል፤ ድጋፍም ያበረክታል፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ መንግሥት የዚህ ዓይነት የተለየ ተሰጥኦና ተውህቦ ያላቸው ተማሪዎች ይህን ችሎታቸውን ይበልጥ ለማዳበር እንዲያስችሏቸው ተብለው በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች እንዲማሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፷፭. የመንግሥት ተግባርና ኃላፊነት

፩/ በሁሉም ዕርከኖች በሚገኙ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት መንግሥት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በተለይ ቀጥሎ ባሉት ጉዳዮች ላይ መመሪያ ያወጣል:-

(ሀ) ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ አጠቃላይ ትምህርት የሚወሰደው ጊዜ፣

(ለ) በትምህርት አሠጣጥ ሂደቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርት አቀባበል የሚለካበት ሁኔታ፣

(ሐ) ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ማሟላት ስለሚገባቸው የብቃት ደረጃ፣

(መ) ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ ተግባራዊ ስለሚደረገው ሥርዓተ ትምህርት፣

## 64. About Students with Special Talents and Gifts

1/ The government pays special attention to students who have special talents and gifts and need attention and inspection to further develop this potential; it also provides support. The details are determined by the Directive issued by the Ministry.

2/ The government can enable students with such special talents and gifts to study in schools established to further develop these skills.

## 65. Duties and Responsibilities of the Government

1/ The government Provides appropriate support to students with special needs in all levels of general education institutions.

2/ The Ministry will issue specific Directive on the following issues:

a) The duration of general education for students with special needs,

b) The measurement of students with special needs' reception in the educational process,

c) Qualification standards for schools providing education for students with special needs,

d) Curriculum implemented for students with special needs,

https://ethiodata.et/

(ሠ) የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሊሰጣቸው ስለሚገባ ተማሪዎች አመዳደብና በየምድቡ ላሉትም ስለሚያስፈልገው የተለየ አገልግሎት፣

(ረ) ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርትን የሚያበረታታ መመሪያ፣

(ሰ) እያንዳንዱ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ሲባል በተለይ የተቋቋመ ወይም በአካቶ ትምህርት አሰጣጥ እነዚህን ተማሪዎች ተቀብሎ የሚያስተምር የትምህርት ተቋም ምቹ የትምህርት አካባቢ፣ አስፈላጊ የሰው ኃይል፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የትምህርት መሣሪያዎችንና ቁሳቁስ በማሟላት ረገድ መውሰድ ስላለበት እርምጃና ስለሚከተለው ዘዴ፣

(ሸ) ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ችግር በተመለከተ የሥራ አፈጻጸሙን በመከታተልና በመገምገም የመማሪያ ሥፍራዎችንና የትምህርት አገልግሎትን አስመልክቶ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ሊቀርብ ስለሚችልበት ሁኔታ፣

፫/ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረገው ሥርዓተ ትምህርት በተቻለ መጠን ከሀገር አቀፉ ሥርዓተ ትምህርት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## የጎልማሶች ትምህርት

### ፷፮. የጎልማሶች ትምህርት መርሆዎች

የጎልማሶች ትምህርት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል:-

፩/ የትምህርት ዕድል በላገኙ ወይም ትምህርታቸውን ባቋረጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት ባደረገ መልክ የተሳታፊዎቹን የተለየ ፍላጎት ያገናዘበ፣

e) Classification of students who should be given special needs education and the special services required for each category,

f) A guide to promoting education for students with special needs,

g) Steps and methods to be taken by each educational institution specially established for students with special needs or accepting and teaching these students through Inclusive education, in providing a comfortable learning environment, necessary personnel, classrooms, educational equipment, and materials,

h) Regarding the problem of students with special needs, by monitoring and evaluating work performance, regarding issues that should be addressed regarding learning places and education services, and submitting a decision proposal to the government,

3/ The curriculum implemented for students with special needs should align with the national curriculum as much as possible.

## Part Eleven
## Adult Education

### 66. Principles of Adult Education

Adult education shall be based on the following principles:

1/ Considering the specific needs of participants, focusing on sections of society who have had access to education or who have dropped out of school,

https://ethiodata.et/

፪/ በግል የትምህርት አቀባበላቸውና በማኅበራዊ ተሳትፎአቸው ረገድ የትምህርቱ ተሳታፊዎች ትምህርቱን በመከታተል ረገድ በሚኖራቸው ብቃትና ጽኑ ፍላጎት፣

፫/ የትምህርት ፍላጎትንና ማኅበራዊ ተሳትፎን በተመለከተ ተገቢውን ማነቃቂያ ማድረግ፣

፬/ እየተሳተፈ ባለበት የትምህርት ሂደት እያንዳንዱ ጎልማሳ ከራሱ ተሞክሮ በመነሳት ተማሪም አስተማሪም ሊሆን ስለመቻሉ ተገቢውን ዕውቅና መስጠት፣

## ፷፯. የጎልማሶች ትምህርት ዓላማዎች

፩/ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ዓላማ ዕድሜያቸው ከ፲፭ ዓመት በላይ የሆኑና ምንም ዓይነት መደበኛ ትምህርት ያላገኙ ወይንም መደበኛ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሰዎች ጥራትና ተገቢነት ባለው የትምህርት አሰጣጥ ሂደት የማንበብና የመጻፍ እንዲሁም የማስላት ዕውቀትና ክህሎት እያገኙ ቀጣይ ትምህርቶችን በመከታተል በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በዕቅድ፣ በተገቢው ድርጅትና ቅንጅት የታገዘ የትምህርት አሰጣጥን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

፪/ በሁሉም ዕርከኖች የሚሰጡ የጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና መርሐ ግብሮች በመንግሥት እየተቀረጹ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ መርሐ ግብሮች የሚቀረጹት የተሳታፊዎቹን ሕይወት ለዘለቄታው በተሻለ መንገድ ለመለወጥ በሚያስችል መልክ ነው፡፡

፫/ የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብሮች ሲቀረጹ በተለይ ጠረፋማ ለሆኑ አካባቢዎችና በመሠረተ ልማት አቅርቦት እጥረት ምክንያት በትምህርት ተደራሽነት ረገድ በአንጻራዊ ሁኔታ ኋላቀር በሆኑ አካባቢዎች ላይ ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

2/ Participants in the course have the ability and strong desire to attend the course in terms of their acceptance of education and their social participation,

3/ Providing appropriate stimulation regarding educational needs and social participation,

4/ Recognizing that each adult can be both a student and a teacher based on their own experience in the educational process they are participating in,

## 67. Objectives of Adult Education

1/ The purpose of basic education for adults is to enable people over the age of 15 who have not received any formal education or who have dropped out of formal education to acquire the knowledge and skills of reading, writing, and computing through quality and appropriate education. Continuing education aims to make them active participants in various social and economic activities, supported by planning, appropriate organization, and coordination.

2/ Education and training programs for adults at all levels will be designed and implemented by the government to positively change participants' lives in a lasting way.

3/ Attention will be given to coastal areas and areas relatively backward in terms of access to education due to a lack of infrastructure when designing adult education programs.

https://ethiodata.et/

፬/ የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብሮች ከመደበኛው መርሐ ግብር ጋር እኩል ዕውቅና ይኖረዋል፡፡

**፷፰. <u>የጎልማሶች ትምህርትን ተግባር ተኮር ስለማድረግ</u>**

፩/ ለቀን ተቀን ኑሯቸው የሚረዳቸውን ዕውቀትና ክህሎት ለመቅሰም ወይም የሙያ ብቃታቸውንና ምርታማነታቸውን የበለጠ በማሳደግ የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ከጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት መርሃ ግብር በተጨማሪ በሙያ ክህሎት ማበልፀጊያ ሥልጠና እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

፪/ የግል ባለሀብቶች የጎልማሶች የመማሪያ ጣቢያዎችንና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከላትን እንዲያቋቁሙ መንግሥት ያበረታታል፡፡

፫/ የተግባር ተኮር የጐልማሶችን ትምህርት የሚያስተባብር አካል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል፡፡

**፷፱. <u>የጎልማሶች ትምህርት ጥራትና አግባብነት</u>**

፩/ የጎልማሶች ትምህርትን አስመልክቶ የሚቀረጹ መርሐ ግብሮች ለትምህርቱ ጥራትና ተገቢነት አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡ የጎልማሶች ትምህርት ይዘት በተጠቃሚዎቹ ፍላጎትና አቅም ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ይህም በመሆኑ መርሐ ግብሩ የሚቀረጸው ለተሳታፊዎች አጠቃላይ ትምህርት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን እንደየዝንባሌያቸውና እንደየፍላጎታቸው ለቀጣይ የሙያና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲዘጋጁ ለማድረግም ጭምር ነው፡፡

4/ Adult education programs will receive the same accreditation as regular programs.

**68. <u>Enhancing Adult Education Through Action-Oriented Approaches</u>**

1/ In addition to basic education programs, adults will participate in career skills enhancement training to acquire knowledge and skills that will help them in their daily lives or increase their professional skills and productivity to have a better life.

2/ The government encourages private investors to establish adult learning centers and skill development centers.

3/ A coordinating body for action-oriented adult education shall be established by regulation of the Council of Ministers.

**69. <u>Quality and Relevance of Adult Education</u>**

1/ Plans for adult education should focus on quality and appropriateness, with content based on users' needs and abilities. Programs are designed not only to provide general education but also to prepare participants for further career and higher education according to their inclinations and needs.

https://ethiodata.et/

፪/ የመምህራን ማሠልጠኛ መርሐ ግብሮች የጎልማሶች ትምህርትን የሚመለከቱ ኮርሶችን የሚያካትቱ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ኮርሶችም የጎልማሶችን ማኅበራዊ አቋምና ቤተሰባዊ ኃላፊነት ከግምት አስገብተው ይቀረጻሉ፡፡

፫/ በጎልማሶች ትምህርት አሰጣጥ ጠቀሜታ ላይ የሚውሉ የትምህርት መሣሪያዎችና የትምህርት ቁሳቁስ እንዲሁም የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ የሚመለከት መመሪያ በሚኒስቴሩ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

**፸. <u>የጎልማሶች ትምህርት የሚሰጥበት ጊዜና ሥፍራ</u>**

፩/ የጎልማሶች ትምህርት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ ለዚሁ ተግባር ሲባል የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማእከል፣ በሠራተኞች ማኅበራት፤ በከተሞች፣ ቀበሌዎች፣ በበይነ-መረብ፣ በርቀት ወይም በሌሎች አካላት በተዘጋጁና ደረጃቸውን በጠበቁ ማዕከላት ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጎልማሶች ትምህርት በሥራ ቦታ፣ በማኅበረሰብ ማዕከላት፣ በቤተሰብ ውስጥ ወይም ሌሎች የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም መደበኛ ባልሆነ መልክ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ የጎልማሶች ትምህርት የጊዜ ርዝመት፣ የትምህርት ዓይነቶች ቅደም ተከተል፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ሰዓታት እንዲሁም የትምህርት ክትትል ምዘናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ፍላጎቶቻቸውንና አቅማቸውን በማገናዘብ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ Teacher training programs should include courses in adult education designed considering the social status and family responsibilities of adults.

3/ Directive regarding educational tools, materials, and information and communication technology of Adult education will be issued by the Ministry.

**70. <u>Time and Place of Adult Education</u>**

1/ Adult education is provided in regular schools, farmers' institutions, workers' unions, cities, kebeles, internet, remote areas, or other entities.

2/ Subject to the provisions of Sub-Article (2) of this article, adult learning may be provided non-formally in the workplace, community centers, in the family, or using other technological options.

3/ The duration of adult education, sequence of subjects, weekly and daily hours of education, and assessment of educational monitoring are determined by Directive s issued by the Ministry, considering participants' needs and abilities.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አሥራ ሁለት

## የትምህርት ፍትሐዊነት

### ፸፩. የትምህርት ፍትሐዊነት መርሆዎች

፩/ የትምህርት ዕድልን ለማመቻቸት ሲባል የሚቀረጹ መርሐ ግብሮች ሁሉ ከተለያዩ ማኅበረሰቦች የሚመጡ ተማሪዎችን በእኩልነት ተጠቃሚ በማድረግ የትምህርት አሰጣጡ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

፪/ የትምህርት ፍትሐዊነት በተለይ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል:-

(ሀ) በጾታ፣ በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በቋንቋ፣ በተወላጅነት፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በዕድሜ ወይም በቡድናዊ ቅርርብ ላይ በመመሥረት የሚፈጸሙ ልዩነቶችና መድሏዊ አሠራሮችን ማስወገድ፣

(ለ) ለሁሉም እኩል ዕድሎችን ማመቻቸት በተለይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሌሎቹ ጋር በእኩል ደረጃ በትምህርት ሥርዓቱ ተጠቃሚ ወደሚሆነበት ደረጃ ከፍ ማድረግ፣

### ፸፪. ለሴቶች ስለሚሰጥ የትምህርት ድጋፍ

፩/ ሴቶች በትምህርቱ ዘርፍ በእኩልነት እንዲሳተፉና በትምህርታቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

፪/ በአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በሴት ተማሪዎችና መምህራን ላይ ማንኛውም ዓይነት መድሏዊ ልዩነት እንዳይፈጸምና ሴቶች ከትንኮሳና ከሌሎችም ዓይነት ጥቃቶች እንዲጠበቁ ለማድረግ ሚኒስቴሩ በትምህርት ተቋማት ጾታዊ ጥቃት ለመከላከል የሚስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

## Part Twelve

## Educational Equity

### 71. Principles of Educational Equity

1/ All programs designed to facilitate educational opportunities will be implemented fairly, benefiting students from different communities equally.

2/ Educational equity focuses particularly on the following issues:

a) Eliminating differences and discriminatory practices based on gender, race, ethnicity, language, origin, color, religion, disability, age, or group affinity,

b) Facilitating equal opportunities for all, especially sections of society that have been historically left behind, to a level where they can benefit from the education system on an equal basis with others.

### 72. Educational Support for Women

1/ Special support will be provided to women according to Directives given by the Minister at different times to enable them to participate equally in the field of education and succeed in their studies.

2/ In order to prevent any form of discrimination against female students and teachers in the general education system and to protect women from harassment and other forms of violence, the Minister will issue Directives to prevent sexual violence in educational institutions;

https://ethiodata.et/

፫/ ሴት መምህራንን በብዛት ለማፍራት እና ወደ ትምህርት አመራርነት ለማምጣት ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፫. <u>ለገጠር ትምህርት ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>**

፩/ መንግሥት አጠቃላይ ትምህርት በገጠር እንዲስፋፋ የተለየ ትኩረት ያደርጋል፤ በዚህም ለገጠር ትምህርት ቤቶች መሠረታዊ ግብአቶች መሟላታቸውንና ትምህርቱም ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፪/ የትምህርት አገልግሎቶች በገጠርና በተለይም ጠረፋማ በሆኑ አካባቢዎች እንዲስፋፉ የተለየ ትኩረትና ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ ትምህርቱ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በማተኮር ይካሄዳል:-

(ሀ) ገበሬዎች ባሏቸው የማምረቻ መሣሪያዎች በአግባቡ በመጠቀም የበለጠ ምርታማ እንዲሆኑ ማድረግ፣

(ለ) የገበሬዎችን የሥራ ቅልጥፍናና የሀብት አጠቃቀም የበለጠ ማሳደግ፣

(ሐ) ገበሬዎችን ከዘመናዊ የአመራረት ዘዴዎች ጋር በማስተዋወቅ በተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማብቃት፣

(መ)የገበሬዎችን የአካባቢ እንክብካቤ፤ የግልና የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅና የቁጠባ ባህል ማበልፀግ፣

**፸፬. <u>በአርብቶ አደር አካባቢዎች ስለሚሰጥ ትምህርት</u>**

፩/ መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢ ባሉ የትምህርት ሥርዓት አተገባበር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመሙላት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3/ Special support will be provided to attract female teachers in large numbers and bring them into the leadership position in the education sector, the details of which shall be determined by the Directives issued by the Ministry.

**73. <u>Support for Rural Education</u>**

1/ The government will pay special attention to promoting general education in rural areas, ensuring that basic resources for rural schools are met and that education meets standards.

2/ Special attention and support will be given to expanding various educational services in rural areas, especially in coastal areas. the details determined by the Directive.

3/ The education will focus on the following issues:

a) Enhancing farmers' productivity by proper utilization of production equipment,

b) Increasing farmers' work efficiency and resource utilization,

c) Empowering farmers with improved production equipment by introducing them to modern production methods,

d) Environmental care for farmers; Enriching the culture of personal and environmental cleanliness and savings,

**74. <u>Education in Pastoral Areas</u>**

1/ The government provides special support by filling gaps in the implementation of the education system in pastoral areas.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አዋጅ የትምህርት ደረጃንና ጥራትን በተመለከተ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጥ ሥርዓተ ትምህርት የነዋሪዎቹን የኑሮ ዘይቤ ደረጃ በደረጃ በበጎ መልኩ ለመለወጥ እንዲያስችል ተደርጎ ይቀረጻል፡፡

፫/ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አጠቃላይ ትምህርት አካላት በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠው ትምህርት ከመደበኛው ትምህርት ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፬/ መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች አጠቃላይ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ የተለያዩ የትምህርት አቅርቦት ስልቶችን ይነድፋል፣ አተገባበሩ ላይም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፭/ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኙ ሕፃናት የኅብረተሰቡን እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ በተንቀሳቃሽ ወይም በከፊል ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

፮/ ለተንቀሳቃሽ ትምህርት ተቋማት የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ አገልግሎቶች አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት ይቀርባሉ፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ያቋቁማል፡፡

፯/ ሚኒስቴሩ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚካሄዱ የትምህርት አቅርቦት ስልቶችና አተገባበሮችን የሚመለከት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ ውጤቱን ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፣ የመፍትሔ ሀሳቦችንም ያቀርባል፡፡

2/ The curriculum provided in pastoral areas will be designed to facilitate a gradual transformation in the residents' way of life, by the provisions of this proclamation regarding the level and quality of education.

3/ Government general education bodies at any level must ensure that education in pastoral areas is equivalent to regular education.

4/ The government will design various education delivery strategies to provide general education to all in pastoral areas, monitoring and supporting implementation.

5/ Children in pastoral areas will attend education in mobile or semi-mobile schools while living with their families based on social movement.

6/ Teaching services needed for mobile education institutions are provided by appropriate government bodies; When necessary, the government also establishes boarding schools in pastoral areas.

7/ The Ministry conducts research and studies regarding education delivery strategies and applications in pastoral areas; Communicates results to stakeholders and proposes solutions.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አሥራ ሦስት

## መንግሥታዊ ስላልሆኑ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት መሰረታዊ መርሆዎች

**፸፭. መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማትን የሚመለከቱ ጠቅላላ ደንቦች**

፩/ አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት በግል ትምህርት ቤትነት፣ በሲቪል ማኅበራት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ የውጭ ሀገር ማኅበረሰቦች ትምህርት ቤትነት፤ በውጭ ሀገራት ባሉ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤትነት፤ በዓለም አቀፍ ትምህርት ቤትነት፤ በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች አካላት ተመሥርተውና ለትምህርት ቤትነት የሚያበቁ መስፈርትን በመሟላት የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡

፪/ መንግሥታዊ ያልሆነ አጠቃላይ የትምህርት ተቋም የራሱ የሆነ የገንዘብ ምንጭና ነጻ አስተዳደር ያለው፣ ገቢውንም ከተማሪዎች ክፍያ፣ ከስጦታ፣ ወይም ከኢንቨስትመንት ትርፍ የሚያገኝና ይህን ነጻነቱን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ድርጅታዊ አወቃቀር ሊኖረው ይገባል፡፡

፫/ መንግሥታዊ ያልሆኑ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የትምህርት ክፍያ ግዴታን እስከተወጡና ወደትምህርት ቤቱ ለመግባት የሚያስፈልገውን አካዳሚያዊ መስፈርት እስካሟሉ ድረስ በተማሪዎች መሀል ማናቸውንም ልዩነትና መድሏዊ አሠራር ከመፈጸም መታቀብ አለባቸው፡፡

## Part Thirteen

## Non-governmental Educational Institutions General Principles

**75. General Rules on Non governmental Institutions**

1/ Non-governmental educational institutions that provide general education, such as private schools, civil associations, schools for foreign communities living in Ethiopia, Ethiopian community schools in foreign countries, ,international schools, schools ownd by religious institutions or established by other bodies according to Directives issued by the Ministry and must be registered by fulfilling school criteria.

2/ A non-governmental general education institution, having its financial resources and independent management, and receiving income from student fees, gifts, or investment profits, must have an organizational structure allowing proper use of this independence.

3/ Non-governmental general education institutions must refrain from any discrimination between students as long as they fulfill tuition fee obligations and academic requirements.

https://ethiodata.et/

፬/ መንግሥታዊ ያልሆኑ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ሊያስከፍሉ የሚገባቸውን የትምህርት ቤትና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን ጣሪያ በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡ ይህ መመሪያ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ታሳቢ ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት በየሦስት ዓመቱ ይስተካከላል፡፡

፭/ መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት ይህን አዋጅ መተላለፋቸው ሲረጋገጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት አግባብ ባለው አካል እርምጃ ይወሰዳል፡፡

**፸፮. <u>የግል ትምህርት ቤት ማቋቋም ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>**

፩/ የሚከተሉት ግለሰቦች ወይም የንግድ ማኅበራት የግል ትምህርት ቤት ማቋቋም አይችሉም፡፡

(ሀ) በፍርድ የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ወይም ዕዳ መክፈል ባለመቻሉ የተነሳ ከባለገንዘቦቹ ጋር ለመደራደር ያመለከተ ሰው፣

(ለ) ትምህርት ቤቱን ለማቋቋም ፍቃድ የሚጠይቀው አመልካች ትምህርት ቤቱን ለማቋቋም ድርሻ ያለው የንግድ ድርጅት ወሳኝ ከሆኑ አባላት አንዱ በወሲባዊ ጥቃት ወይም በሌሎች በሕፃናት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተወሰነበት፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ድንጋጌ ወንጀሉን ፈፅሞ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ አግባብ ባላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የተሰየመ ሰውን አይመለከትም፡፡

4/ The Ministry may issue Directives regarding the ceiling of school and other service fees charged by non-governmental general education institutions. This Directive is revised every three years, taking into account economic and other considerations.

5/ When non-governmental educational institutions violate this Proclamation, the appropriate body may take action in accordance with Regulations issued by the Council of Ministers.

**76. <u>Prohibition of Establishing a Private School</u>**

1/ The following individuals or business associations cannot establish a private school.

a) A person declared bankrupt by a court or who has applied for settlement with creditors due to inability to pay debts,

b) The applicant seeking permission to establish the school has been found guilty of sexual abuse or other crimes against children by one of the significant members of the business organization with a share in establishing the school,

2/ The provision referred to in Sub-Article (1) of this Article shall not apply to a person who has been reinstated in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code after committing the offense and pleading guilty

https://ethiodata.et/

**፸፯. የግል ትምህርት ቤት ለማቋቋም መሟላት ያለባቸው ተጨማሪ መስፈርቶች**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥ የግል ትምህርት ቤት የሚከተሉትን ተጨማሪ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤

(ሀ) በአግባቡ የተመዘገቡና ፈቃድ ያላቸው መምህራን፣

(ለ) በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባላቸው የክልል አካላት የጸደቁ ሥርዓተ ትምህርቶችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚሰጥ ማረጋገጫ፣

(ሐ) የአለምአቀፍ ትምህርት ቤቶች የሚጠቀሙበት ስርአተ ትምህርቱ ከተቀዳበት ሀገር የጸደቀና ስራ ላይ ያለ መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ፣

(መ) ተገቢውን የአካባቢ ደህንነት፣ የጤናና የሕንፃ ደረጃ የጠበቀ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ፣

(ሠ) ሚኒስቴሩ ያወጣውን ስታንዳርድ የጠበቁ የመማር፣ ማስተማር መሣሪያዎች፣

(ረ) የተማሪዎች የተሟላ ሪከርድ፣

(ሰ) ለትምህርት ቤቱ አገልግሎት የሚውለው ሕንፃ የኪራይ ከሆነ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ለዚሁ አገልግሎት ለማዋል የሚያስችል አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የኪራይ ውል፣

(ሸ) የትምህርት ቤቱን መምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ቢያንስ የስድስት ወር ደመወዝ ክፍያ ለመሸፈን የሚችልና በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠና በባንኩ የተረጋገጠ ሒሳብ፣

**77. Additional Requirements to Establish a Private School**

1/ A private school providing general education must meet the following additional requirements, subject to the provisions of Article 22 of this Proclamation;

a) Duly registered and licensed teachers,

b) Certification to implement curricula approved by the Ministry or relevant regional bodies,

c) Proof that the curriculum used by international schools is approved and in use in the country where the curriculum was taken,

d) School premises meeting appropriate environmental safety, health, and building standards,

e) Learning and teaching tools meeting standards issued by the Ministry.

f) Complete student records,

g) If the building used for the school is rented, a lease agreement certified by the appropriate body for at least two years,

h) A closed bank account covering at least six months' salary of the school's teachers and other employees, certified by the bank,

https://ethiodata.et/

፪/ አንድ የግል ትምህርት ቤት የገቢ ምንጮቹንና የወጪ ዝርዝሩን የሚያመለክት የትምህርት ዘመኑን በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

## ፸፰. የግል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር

፩/ ያልተማከለ አስተዳደርን የሚመለከቱት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ በግልና በሌሎችም መንግሥታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ላይም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጸው አጠቃላይ ሃሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ የግልና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት የሚከተሉትን በአባልነት የያዘ የትምህርት ቤት ኮሚቴ ይኖራቸዋል:-

(ሀ) የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ያልሆኑ ወላጆች ተወካዮች፣

(ለ) የትምህርት ቤቱ መምህራን ተወካዮች፣

(ሐ) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን የተማሪዎች ተወካዮች፣

(መ) በትምህርት ቤቱ አጎራባች አካባቢዎች ያሉ የሀገር ሽማግሌዎች ተወካዮች፣

(ሠ) አግባብ ባለው አካል በሚወስነው መሠረት የሚወከሉ ሌሎች አባላት፣

፫/ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የኮሚቴው ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

፬/ የትምህርት ቤቱ ኮሚቴ በትምህርት ቤቱ ዙሪያ ያሉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ የወላጆችን ስጋቶች፣ በትምህርት ቤቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ማኅበረሰብ የሚጠብቃቸውን አገልግሎቶች እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እያጠና ይመረምራል፣ የዕቅድ አፈጻጸሞችንም ይገመግማል፡፡

2/ A private school must prepare a budget for the academic year, indicating sources of income and expenses, and submit it to the concerned body.

## 78. Management of Private Schools

1/ The provisions of this Proclamation regarding decentralization apply to the administration of private and other non-governmental schools.

2/Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) of this Article Private and other non-governmental educational institutions must have a school committee consisting of :

a) Parents' representatives who are not school employees,

b) The school's teacher representatives,

c) In middle level schools, student representatives,

d) Representatives of elders in the school's neighboring areas,

e) Other members as determined by the Council,

3/ The principal acts as secretary of the committee.

4/ The school committee studies and examines school-related issues, student needs, parental concerns, expected community services, and evaluates plan performance.

https://ethiodata.et/

፭/ አንድ የግል ትምህርት ቤት የሚካሄደውና የሚተዳደረው መሥራቹ አካል በተቋቋሙበት የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነው፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡም ይህን አዋጅና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎችንና ደንቦችን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡

፮ የግል ትምህርት ቤቶች ማኅበር የትምህርት ዘርፉን በአዎንታዊ መልኩ በሚደግፉበት አግባብ እንዲደራጁ መንግሥት ያበረታታል፡፡

፯ የግል ትምህርት ቤቶች ወላጅ እና ተማሪዎች ኮሚቴዎች የአጠቃላይ ትምህርት ወላጅ ኮሚቴዎች ምክር ቤት አባላት ሆነው እንዲሠሩ የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴሩ ይወጣል፡፡

**፸፱. <u>በሌሎች መንግሥታዊ ባልሆኑ አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ደንቦች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ስለግል ትምህርት ቤቶች የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው አጠቃላይ ትምህርት በሚሰጡ በሌሎች መንግሥታዊ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት ላይም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ድንጋጌ የሚከተሉትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶችን ያካትታል፡፡

(ሀ) የሲቪል ማኅበራት ትምህርት ቤቶች፤

(ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ በሚቋቋሙ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች፤

(ሐ) በውጭ ሀገራት በሚቋቋሙ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች፤

(መ) ኢትዮጵያ ውስጥ በሚቋቋሙ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች፤

(ሠ) በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት በሚካሄዱ ትምህርት ቤቶች፤

5/ A private school is conducted and managed according to the articles of association of the founding body. Bylaws must comply with this proclamation and other relevant laws and regulations.

6/ The government encourages private school associations to support the education sector positively.

7/ The Ministry issues an instruction allowing parent and student committees of private schools to act as members of the General Education Parent Committee Council.

**79. <u>Other Non-governmental General Education Institutions Applicable Regulations</u>**

1/ Regulations described in Article 83 of this proclamation about private schools apply to other non-governmental educational institutions providing general education as appropriate.

2/ The provision referred to in Sub Article (1) of this article includes the following non-governmental schools.

a) Civil society schools;

b) Foreign community schools established in Ethiopia;

c) Ethiopian community schools established in foreign countries;

d) International schools established in Ethiopia;

e) Schools owned by religious institutions;

https://ethiodata.et/

**፹. <u>የፈቃድና እውቅና አሠጣጥ</u>**

፩/ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ የግል ትምህርት ቤቶችን፣ የሲቪል ማኅበራት ትምህርት ቤቶችንና በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የሚካሄዱ ትምህርት ቤቶችን የመመዝገብ፣ ፈቃድና ዕውቅናም የመሰጠት ሥልጣን አላቸው፡፡

፪/ መንግሥታዊ ያልሆኑ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ፈቃዳቸውን በየሁለት ዓመቱ አግባብ ባለው አካል የማሳደስ ግዴታ አለባቸው፡፡

፫/ አዲስ የተቋቋመ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋም የዕውቅና ጥያቄ ማመልከቻውን አግባብ ላለው አካል ካስገባ በኋላ በማመልከቻው የተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች ተቋሙ ከመመዘኛ መስፈርቱ ውስጥ ሰማንያ አምስት በመቶ (፹፭/፻) ወይም ከዚያ በላይ ያሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ ለአንድ ዓመት የሚያገለግል የቅድመ ዕውቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፬/ ትምህርት ቤቱ የቅድመ ዕውቅና ፈቃድ በተሰጠው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የመመዘኛ መስፈርቱን ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ ሙሉ የዕውቅና ፈቃድ ያገኛል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕውቅና ፈቃድ ያላገኘ ተቋም አጠቃላይ ትምህርት የመስጠት ሥራ መሥራት አይችልም፡፡

**፹፩. <u>የማመልከቻ አቀራረብ ሥርዓት</u>**

፩/ አጠቃላይ የትምህርት ተቋም ለማቋቋም ፍላጎት ያለው የተፈጥሮ ሰውም ሆነ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም ማመልከቻውን አግባብ ላለው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

**80. <u>Grant of License and Accreditation</u>**

1/ Regional education offices have the authority to register, license, and recognize private schools, civil society schools, and schools owned by religious institutions based on Directives issued by the Ministry.

2/ Non-governmental institutions of general education are required to renew their licenses every two years with the appropriate body.

3/ After a newly established general education institution submits its application for accreditation to the appropriate body, if it is confirmed that the institution meets eighty-five percent (85%) or more of the criteria listed in the application, it will be granted a one-year pre-accreditation license.

4/ The school will receive a full accreditation license when it fully meets the criteria within one year of receiving the pre-accreditation license.

5/ According to this article, an institution that has not obtained a accreditation license cannot provide general education.

**81. <u>Application Submission System</u>**

1/ A natural person or a person authorized by law interested in establishing a general education institution can submit the application to the relevant body by paying the specified service fee.

https://ethiodata.et/

፪/ የግል ትምህርት ቤቶች፣ የሲቪል ማኅበራት ትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች፣ በተመለከተ የዕውቅና ፈቃድ ለመጠየቅ ማመልከቻ ለወረዳ/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የሚቀርብ ሲሆን፤ አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላቱ የማረጋገጥ እና ፍቃድ መስጠት የክልል የትምህርት አስተዳዳር አካላት ኃላፊነት ይሆናል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ ቢሮው የተጠየቀውን ፈቃድ የመስጠት ወይም የመመዘኛ መስፈርቶች ያልተሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ የተጠየቀውን ፈቃድ የመከልከል ሥልጣን አለው፡፡

፬/ ጥያቄው የቀረበለት አካልም ማመልከቻውን ከመዘገበ በኋላ በሕግ የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውንና ተፈላጊ ዝርዝር ሰነዶች ተያይዘው መቅረባቸውን በማረጋገጥ የተጠየቀውን የቅድመ ዕውቅና ወይም የዕውቅና ማረጋገጫ ፈቃድ ጥያቄው በቀረበለት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተገቢው ምላሽ መሰጠት አለበት፡፡

፭/ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት በመጠየቅ ውሳኔው በደረሰው በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

2/ Private schools, schools established by civil society organizations, and schools owned by religious institutions shall be required to submit an application for accreditation. Applications shall be submitted to the district/city government education office, and the assurance and licensing of compliance with the requirements shall be the responsibility of the regional educational administrations. The criteria for approval shall be determined by the Directive issued by the Ministry.

3/ The office has the authority to grant the requested license or deny it when it is confirmed that the criteria are not met.

4/ After filing the application, the party to whom the request was submitted must confirm that the requirements set by law have been met, and that the necessary detailed documents have been submitted. An appropriate response must be given within thirty days of the request for pre-accreditation or certification permission.

5/ A person dissatisfied with the decision has the right to submit a complaint to a grievance body established in the office within fifteen days of receiving the decision.

https://ethiodata.et/

፮/ በሁለተኛው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔውን በመቃወም እንደነገሩ ሁኔታ በህግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ፹፪. <u>በማመልከቻው ስለሚገለጹ ፍሬ ነገሮች</u>

አጠቃላይ የትምህርት ተቋም ለማቋቋም ፈቃድ ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች መግለጽ አለበት፤

፩/ የተቋሙን ስምና አድራሻ፣

፪/ የተቋሙን የአስተዳደርና የሥራ አመራር መዋቅር፣ የሥራ አመራር አባላትና የተቋሙን መሥራቾች ስም ዝርዝር ፣ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ፣

፫/ የትምህርት ተቋሙ ዓላማና ግብ፣ የትምህርት አሠጣጥ መርሐ ግብርና የሚሰጡት ትምህርት ዓይነቶች፣

፬/ የመምህራንና የሌሎች ሠራተኞች ቁጥር፣ የትምህርት ደረጃና ብቃት፣

፭/ ያሉት የማስተማሪያ ክፍሎች፣ የትምህርት መሣሪያዎችና የትምህርት ድጋፍ ቁሳቁስ፣ እንዲሁም የገንዘብ አቅም መግለጫ፣

፮/ ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ትምህርት ቢሮዎች የሚያስቀምጧቸው ሌሎች መስፈርቶች፡፡

## ፹፫. <u>የማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶችንና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶችን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፩/ በዚህ ምዕራፍ መንግሥታዊ ስላልሆኑ ትምህርት ቤቶች የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉት ደንቦች እንደአግባብነታቸው በዚህ አንቀጽ ለተመለከቱት አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

6/ A party aggrieved by the second decision may appeal against it to the Federal High Court or the Regional Supreme Court, as the case may be, within one month. The court's decision in the matter shall be final.

## 82. <u>Items to be Specified in the Application</u>

An application for permission to establish a comprehensive educational institution must specify the following details;

1/ Name and address of the institution,

2/ The administrative and management structure of the institution, the list of members of the management and the founders of the institution, their level of education and work experience,

3/ The purpose and goal of the educational institution, the curriculum, and the types of education offered,

4/ Number of teachers and other staff, their level of education and qualifications,

5/ The available teaching units, educational equipment, educational support materials, as well as a regionalment of financial capacity,

6/ Other requirements set by the Ministry or regional education offices.

## 83. <u>Special Provisions Relating to Community Schools and International Schools</u>

1/ Subject to the provisions of this Chapter regarding non-governmental schools, the following Regulations shall apply to the general educational institutions referred to in this Article, as appropriate.

https://ethiodata.et/

፪/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች፣ በውጭ ሀገራት የሚቋቋሙ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች እና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች በሚኒስቴሩ ተመዝግበው ፈቃድና ዕውቅና ያገኛሉ፡፡

፫/ በውጭ ሀገር ማኅበረሰብ የሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ከሚያስፈልጋቸው በጀት በሀገራቸው መንግሥት ፴ በመቶ (፴/፻) የሚደገፉ፤ ቀሪውን ፸ በመቶ (፸/፻) ራሳቸው መሸፈን የሚችሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ማረጋገጫ ማምጣት አለባቸው፡፡ ይህ ማረጋገጫ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና አግባብ ባለው የሰነዶች ማረጋገጫ ባለሥልጣን የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

፬/ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚቋቋሙ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች እና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ከሚመለከተው ሀገር የሥራ ፈቃድ ማምጣት አለባቸው፡፡

፭/ ሥርዓተ ትምህርትን፣ የመምህራን የሙያ ደረጃን እንዲሁም የተማሪዎችን ምዘናን በተመለከተ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በውጭ ሀገሮች በተቋቋሙ የኢትየጵያ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች ላይም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

2/ Foreign community schools established in Ethiopia, Ethiopian community schools established in foreign countries, and international schools established in Ethiopia shall be registered, licensed, and accredited by the Ministry.

3/ 30% (thirty percent) of the budget of schools established by foreign communities is supported by the government of their country, they must provide proof that they can cover the remaining 70% (seventy percent) themselves. This certification must be authenticated by the Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the appropriate document certification authority.

4/ Teachers teaching in foreign community schools and international schools established in Ethiopia must have a work permit from the relevant country.

5/ The provisions of this proclamation regarding the curriculum, professional standards of teachers, and assessment of students shall also apply to Ethiopian community schools established in foreign countries.

https://ethiodata.et/

፮/ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚቋቋሙ የውጭ ሀገር ማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች እና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እየሆነ ያለው ሥርዓተ ትምህርት ከኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት የተለየ ከሆነ አመልካቹ ሥርዓተ ትምህርቱ ከጸደቀበት ሀገር ይህንኑ የሚመለከት ማረጋገጫ ማቅረብና የቀረበውንም ማረጋገጫ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና አግባብ ባለው የሰነድ አረጋጋጭ አካል እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

፯/ ሚኒስቴሩ የተጠየቀውን ፈቃድ የመስጠት ወይም የመመዘኛ መስፈርቶቹ ያልተሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ የተጠየቀውን ፈቃድ የመከልከል ሥልጣን አለው፡፡

፰/ ስለፈቃድ አጠያየቅና ስለዕውቅና አሰጣጥ በዚህ ምዕራፍ አንቀጽ ፹፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ እስከ ፮፣ እንዲሁም አንቀጽ ፹፮ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከቱት አጠቃላይ የትምህርት ተቋማትም እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፹፬. <u>አቻ ግመታ</u>**

፩/ በውጭ ሀገር አጠቃላይ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች አቻ ግመታ በሚኒስቴሩ ይካሄዳል፡፡

፪/ አቻ ግመታን የሚመለከቱ መሠረታዊ መመዘኛዎች ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በጠበቀ መልኩ በሚኒስቴሩ ይወሰናሉ፡፡

6/ If the curriculum implemented in foreign community schools and international schools established in Ethiopia differs from the Ethiopian curriculum, the applicant must submit a certificate from the country where the curriculum was approved and have the submitted certificate registered with the Ministry of Foreign Affairs of Ethiopia and the relevant document verification body.

7/ The Ministry has the authority to grant the requested license or deny it when it is confirmed that the criteria are not met.

8/ In this chapter, Article 81, Sub Article (4) to (6) about the request for permission and the granting of accreditation; Also, the provisions referred to in Article 86 shall be applicable to the general education institutions referred to in this Article as appropriate.

**84. <u>Evaluation of Equvlency</u>**

1/ Equivalency assessment of educational credentials provided by foreign general education institutions will be conducted by the Ministry.

2/ The basic criteria for equivalent assessment are determined by the Ministry in accordance with international standards.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አሥራ አራት

## የትምህርት ፋይናንስ

### ፹፭. የመንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ

፩/ መንግሥታዊ የሆኑ የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት የዜጐችን የትምህርት አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብትን ለማረጋገጥ መንግሥት ተገቢውን በጀት ይመድባል፡፡

፪/ ለትርፍ ተብለው ባልተቋቋሙ የሲቪል ማኅበራት የትምህርት ተቋማት መንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

### ፹፮. የመንግሥት የትምህርት ወጪ የሚሸፈንባቸው ምንጮች

፩/ የሚከተሉት ምንጮች የትምህርት ወጪዎችን ለመሸፈን ተግባራዊ ይደረጋሉ:-

(ሀ) በመንግስት ከሚመደብ በጀት፣

(ለ) በሀገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ተቋማት ለአጠቃላይ ትምህርት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ፣

(ሐ) የፌደራል ወይም የክልል መንግሥታት ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ ምንጮች የሚያገኙት ብድር፣

(መ) ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ትምህርት ቢሮዎች ከሚያበረክቷቸው አገልግሎቶች የሚሰበሰቧቸው ክፍያዎች፣

(ሠ) የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት የራሳቸውን ገቢ በማመንጨት፣ ስጦታ ውርስና የውጭ እርዳታዎችን በማሰባሰብ፣ መንግሥት የሚመድብላቸውን በጀት የማጠናከር ሥራ መሥራት ይችላሉ፡፡

## Part Fourteen

## Education Finance

### 85. Constitutional Obligation of the Government

1/ The government shall allocate an appropriate budget to ensure that governmental general education institutions provide equal access to educational services for all citizens.

2/ The government may provide financial support to non-profit educational institutions. The detailed implementation may be determined by the Directive issued by the Ministry.

### 86. Sources of Government Education Expenditure

1/ The following sources shall be utilized to cover educational costs:

a) From the budget allocated by the government,

b) Financial support for general education in local or international institutions,

c) Federal or regional government loans from domestic or foreign sources,

d) Fees collected from services provided by the Ministry or regional education offices,

e) General education institutions can strengthen the budget allocated by the government by generating their income, collecting donations, and receiving foreign aid.

https://ethiodata.et/

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ትምህርት ቢሮዎች ለትምህርት የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ ሥራዎች የመሥራትና የተሰበሰበውንም ገንዘብ አስቀድሞ በተዘጋጀ ቀመር መሠረት በሚዛናዊነት ማከፋፈል ይችላሉ፡፡

፫/ በማኅበረሰብ ተነሳሽነት የሚደረጉ የትምህርት ድጋፍ ማሰባሰብ ሥራዎች የሚካሄዱት የገንዘብ ድጋፉን እንዲያደርጉ በሚጠየቁት ግለሰቦችና ድርጅቶች ፈቃድና አቅም ላይ በመመሥረት ብቻ ነው፡፡

**፹፯. <u>ሀገር አቀፍ የትምህርት ፈንድ</u>**

፩/ መንግሥት ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ትምህርትን በብቃትና በጥራት ለማዳረስ ያለበትን ግዴታ በሚገባ እንዲወጣ ያስችለው ዘንድ ሀገር አቀፍ የትምህርት ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የፈንዱን ምንጮች የአገልግሎት ክፍያንና አስተዳደር የሚመለከት ዝርዝር ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አሥራ አምስት
## የተማሪዎች መብቶችና ግዴታዎች

**፹፰. <u>የተማሪ መብቶች</u>**

፩/ ማንኛውም ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ተማሪ በመንግሥት ትምህርት ቤት ገብቶ እስከ ፲፪ኛ ክፍል ክፍያ ሳይጠየቅ የመማር መብት አለው፡፡

፪/ ማንኛውም ተማሪ ትምህርቱን በአግባቡ ለመከታተል ይቻለው ዘንድ አስፈላጊ የትምህርት ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት፣ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነቱ እንዲጠበቅለት ሌሎችም መልካም የትምህርት ሁኔታዎች እንዲሟሉለት ይደረጋል፡፡

2/ The Ministry or Regional Education Offices can carry out revenue collection activities for education and distribute the collected money in a balanced manner according to a pre-arranged formula.

3/ Community-led educational support collection activities are conducted only based on the will and capacity of the individuals and organizations asked to provide financial support.

**87. <u>National Education Fund</u>**

1/ A National Education Fund is hereby established to enable the government to fulfill its obligation to deliver education to all sections of society efficiently and with quality.

2/ The Council of Ministers will issue Regulations regarding the service charge and management of the fund sources.

## Part Fifteen
## Rights and Obligations of Students

**88. <u>Rights of Students</u>**

1/ Any student of school age has the right to attend a government schools and study up to the grade 12 free of charge.

2/ Every student will be provided with the necessary educational conditions, physical and mental health, and other conducive educational conditions to enable proper study attendance.

https://ethiodata.et/

፫/ ማንኛውም ተማሪ ከአካላዊ ቅጣት፣ ከሌሎችም በሰብዕናው ዕድገት ላይ ከሚፈጸሙ ጎጂ ድርጊቶች፣ ከኃይል ጥቃትና ከመገለል ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

፬/ ተማሪ መምህሩን የመጠየቅ፣ ሀሳቡን በነጻነት የመግለጽና በተጓዳኝ ትምህርቶች የመሳተፍ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህ ሀሳብን የመግለጽ መብት ከመምህሩ ወይም ከሌሎች ትምህርት ሰጪ አካላት ሀሳብ የተለየ ሀሳብ ማቅረብን ይጨምራል፡፡

፭/ ተማሪዎች በአካዳሚያዊም ሆነ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በሚተላለፉባቸው ውሳኔዎች ላይ ያሉዋቸውን ቅሬታዎች የማቅረብና ለቅሬታዎቹም መልስ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፮/ ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ቤት የምክር አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፯/ ተማሪዎች በተጓዳኝ ትምህርት ክበባት የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

፰/ ተፈላጊው ውክልና ያላቸው የተማሪዎች ተጠሪዎች እንደአስፈላጊነቱ በትምህርት ቤት አስተዳደርና አመራር እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

**፹፱. <u>የተማሪዎች ግዴታዎች</u>**

ተማሪዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል፦

፩/ ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ማንኛውም ሕጻን በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርቱን የመከታተል፣

፪/ የትምህርት ቤት የሥነ ምግባር ደንቦችን፣ ሕጎችንና መመሪያዎችን ማክበር፣

፫/ ትምህርት ቤቱ የሚያወጣውን የጊዜ ሰሌዳ በመከተል ክፍል ገብቶ ትምህርቱን የመከታተል፣

3/ Every student will be protected from physical punishment, other harmful actions on the development of humanity, violence, and isolation.

4/ A student has the right to question the teacher, express thoughts freely, and participate in related lessons. This right to express ideas includes presenting ideas that differ from those of the teacher or other educational institutions.

5/ Students have the right to submit grievances in academic and administrative matters and get answers to them.

6/ Students have the right to counseling at their school.

7/ Students have the right to participate in co-curricular clubs.

8/ Students who have the required representation will participate in school management and leadership as needed.

**89. <u>Obligations of Students</u>**

Students shall have the following obligations:

1/ Any child of school age in government schools, up to the pre-primary level, shall obliged to attend primary and middle-level education,

2/ Every student shall obliged to comply with the school rules, Directives and Regulations,

3/ Following the schedule that the school sets out to go to class and attend school,

https://ethiodata.et/

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ወይም ፫ የተገለጸው አጠቃላይ ሃሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፦

(ሀ) የመታወቂያ ወረቀቱን የመያዝና አግባብ ባላቸው አካላት ሲጠየቅ ማሳየት፤

(ለ) በትምህርት ሰዓት የትምህርት ቤት የደንብ ልብሱንና ባጁን/መለያውን ማድረግ፤

(ሐ) በትምህርት ቤቱ የሰንደቅ ዓላማ ማውጣትና ማውረድ ሥነ ሥርዓት ላይ መገኘት፤

(መ) በፈተና ጊዜ ከሚደረጉ ኩረጃዎችና ሌሎች ዓይነት ያልተገቡ ድርጊቶች መታቀብ፤

(ሠ) በትምህርት ቤት ውስጥና አካባቢ ሲጋራ፣ የአልኮል መጠጦች፣ ጫት ወይም ማንኛውንም አደንዛዥ ዕፅ ይዞ አለመገኘት፣ አለመጠቀም፣ አለመሸጥና አለመግዛት፤

(ረ) ከአካላዊ ድብደባ፣ ከስድብ፣ ከማስፈራራት፣ ከማስገደድ፣ ከዛቻና ከትንኮሳ ድርጊቶች መታቀብ፣ ይህም በተማሪዎች በመምህራንና በሌሎች የትምህርት ቤቱ ባልደረቦች ላይ የሚፈጸሙ መድፈርና ሌሎች ዓይነት የፆታዊ ጥቃቶች የመፈጸም ድርጊቶችን ይጨምራል፤

(ሰ) የማስተማር ሥራውን ወይም ሌሎች የትምህርት ቤቱን እንቅስቃሴ ከሚያውኩ ድርጊቶች መታቀብ፤

4/ Subject to the general idea in Sub Article (1) or (3) of this article, students shall have the following obligation equitably:

a) Possession of the identity document and showing it when requested by the appropriate authorities;

b) Wearing the school uniform and badge/tag during school hours;

c) Attending the flag-raising and lowering ceremony of the school;

d) Abstaining from cheat and other inappropriate activities during exams;

e) Not having, using, selling, or buying cigarettes, alcoholic beverages, chaat, or any drugs in and around the school;

f) Refraining from physical assaults, insults, threats, coercion, harassment, including bullying, and other forms of sexual violence against teachers and other school colleagues;

G) Abstaining from activities that disrupt teaching or other school activities;

https://ethiodata.et/

(ሸ) ስርቆት ወይም ሌላ የማይገባ ድርጊት አለመፈጸም፣ በትምህርት ቤቱ ንብረት ላይ ጉዳት አለማድረስ እንዲሁም የትምህርት ቤቱን፣ የተማሪዎችን የመምህራንና የሌሎችንም ንብረቶች ያለፈቃድና ያለአግባብ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ አለማንቀሳቀስ፤

(ቀ) መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎችን እንዲሁም የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ማክበር፤

(በ) ተማሪዎች የትምህርት ሥርዓቱ ዋነኛ ተጠቃሚዎች እንደመሆናቸው መጠን ዕድሜያቸውና የአስተሳሰብ ብስለታቸው በፈቀደው መጠን በትምህርት ቤት አስተዳደራዊና ሌሎች አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡

## ፺. አስተዳደራዊ እርምጃዎችና ቅጣቶች

፩/ ሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ አኳኋን የሚቀረጹና ለሁሉም የየተቋማቱ ማኅበረሰብ አባላት በቅድሚያ ሊገለጹ የሚገቡ የሥነ ሥርዓት ደንቦችና መመሪያዎች ሊኖሯቸው ይገባል፡፡

፪/ የወንጀል ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላከበረ ተማሪ ትምህርት ቤቱ ባወጣው የሥነ ሥርዓት ደንብ መሠረት ተገቢው እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

h) Not committing theft or other inappropriate acts, not causing damage to the school's property, and not moving the property of the school, students, teachers, and others from one place to another without permission and improperly;

i) Respecting teachers, other education professionals, and school staff;

j) As students are the main beneficiaries of the education system, they should participate in school administration and other general matters as much as their age and maturity allow.

## 90. Administrative Measures and Penalties

1/ All institutions of general education should have formal Directive and Regulations formulated in accordance with this Proclamation and should be explained to all members of the society in advance.

2/ Subject to provisions regarding criminal responsibility, a student who does not comply with the obligations set forth in Article 89 of this Proclamation will be subject to appropriate action according to the disciplinary rules issued by the school.

https://ethiodata.et/

፫/ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት እንዲወገድ የሚደረገው የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የሌሎች የትምህርት ቤቱን አባላት አካላዊና ሥነልቦናዊ ስሜት የሚጎዳ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁንና ደንቡ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፬/ በሥነ ሥርዓት ጥሰት ከትምህርት ቤት የተወገደ ተማሪ ወደ መልካም ጠባይ የተመለሰ መሆኑ ተማሪው ከሚኖርበት የአካባቢ አስተዳደር ማረጋገጫ ሲያቀርብ ወደ ትምህርት ቤቱ ተመልሶ ትምህርቱን እንዲቀጥል ዕድል ይሰጠዋል፡፡

፭/ በሀገር አቀፍ ወይም በክልል አቀፍ ፈተናዎች የመኮረጅ ወይም የማስኮረጅ ወይም ሌላ አግባብ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽም የተገኘ ተማሪ አግባብ ባላቸው አካላት በወጡ ደንቦች መሠረት ተገቢው እርምጃ ይወስድበታል፡፡ ይህ ድንጋጌ ባስኮረጀ፣ ኩረጃ እንዲፈጸም ባስተባበረ ወይም ሁኔታዎችን ባመቻቸ መምህር፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ወይም በሌላ በማናቸውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፺፩. ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት

፩/ የመምህራን ማኅበራት ለአጠቃላይ ትምህርት ሥራው ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግና በተለይም የመምህራን ልማትን በተመለከተ በሚቀረጹ መርሐ ግብሮች የመሳተፍ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3/ A student will be removed from school when it is confirmed that he has committed a serious disciplinary offense that harms the physical and psychological well-being of students, teachers, and other members of the school. However, this rule does not apply to pre-primary school students.

4/ A student who has been removed from school due to disciplinary violations will be given the opportunity to return to school and continue his education when he submits a certificate from the local administration where the student lives, proving that he has returned to good behavior.

5/ Appropriate actions shall be taken against a student who is found to be cheating or assists in cheating or committing other inappropriate actions during regional and national examinations, in accordance with Regulations issued by the relevant bodies. This provision shall apply to a teacher, school employee or any other person who has facilitated, coordinated, or facilitated the execution of cheating.

## 91. Other Education Stakeholders

1/ Teachers' unions have the responsibility to provide necessary support for the general education process, especially participating in plans for teacher development.

https://ethiodata.et/

፪/ ከትምህርት ሥርዓቱ ውጭ ያሉ የመንግሥት አካላት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የጥናትና ምርምር ማዕከላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሥርዓተ ትምህርቱን ለማሻሻል በሚካሄድ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ በትምህርት መሣሪያዎችና በሌሎች ደጋፊ ቁሳቁስ ምርት ሥራዎች፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የጸደቁ ፖሊሲዎችንና መርሐ ግብሮችን መሠረት በማድረግ ለትምህርት የሚያስፈልጉ የገንዘብ ምንጮችን በማፈላለግ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡

## <u>ክፍል አሥራ ስድስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### ፺፪. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፺፫. <u>የቅጣት ድንጋጌዎች</u>

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ ሰው በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወሰዱበት አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

### ፺፬. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል ደንብ ያወጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

2/ Government bodies outside the education system, higher education institutions, research centers, non-governmental organizations, and professional associations are encouraged to actively participate in finding the financial resources needed for education, according to nationally approved policies and programs, in research activities to improve the curriculum, educational equipment, and other supporting material production activities, in accordance with the Directives issued by the Ministry.

## <u>Part Sixteen</u>
## <u>Miscellaneous Provisions</u>

### 92. <u>Duty to Cooperate</u>

Everyone is obliged to cooperate in the execution of this Proclamation.

### 93. <u>Criminal Liabilities</u>

A person who violates the provisions of this Proclamation shall be punished according to criminal law, subject to the provisions of this Proclamation and the administrative measures to be taken in accordance with it.

### 94. <u>Power to Issue Directive and Regulations</u>

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations to implement this Proclamation.

2/ The Minister shall issue Directive to implement this Proclamation and the Regulations issued pursuant to Sub Article (1) of this Article.

https://ethiodata.et/

፫/ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ እስካልሆኑ ድረስ ክልሎች አጠቃላይ ትምህርትን የተመለከቱ የማሟያ ሕጎችን ማውጣት ይችላሉ፡፡

**፺፭. <u>ከዚህ አዋጅ ጋር ስለማይስማሙ ሕጎች</u>**

ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የተጣጣመ ካልሆነ ይህ አዋጅ በሚገዛቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፺፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

አጠቃላይ ትምህርትን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም ሲሰራባቸው የነበሩ ደንቦች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፺፯. <u>አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ Regional governments may enact supplementary laws concerning general education, as long as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation.

**95. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

Any law, Regulation, Directive, or customary practice inconsistent with this Proclamation shall not apply to the matters governed by it.

**96. <u>Transitional Provision</u>**

The previous Regulations regarding general education shall continue in force until they are superseded by Regulations issued under this Proclamation.

**97. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall be effective from the date of its publication in the Federal Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 10th Day of April, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF**

https://ethiodata.et/